አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHIINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ
## የተማሪ መጽሐፍ



## ፫ኛ ክፍል

# አማርኛ

## እንደ መጀመሪያ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## ፫(3)ኛ ክፍል

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

አዘጋጅ
ባንቲሁን አለሙ ዘለለው
አዲስ ሲሳይ እዛዝ
ፋናዬ አሰፋ ቢቂላ
ገምጋሚና አርታኢዎች
መስፍን ደፈረሱ ወ/መድኅን
ትንቢት ግርማ ኃይሉ
ፋሲል ብዙነህ በቀለ
የጥራት ተቆጣጣሪንና ገምጋሚ
ፍሬሕይወት አሰፋ ከበደ
አስተባባሪ
ጌታቸው ታለማ አጥናፉ
አቀማመጥ እና ሥዕል
እንጦጦ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ(TMS)

© የመጽሐፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት 2014 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ ነው።

**ምስጋና**

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ ላደረጉት ከፍተኛ ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ ላደረጉት ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ዘላለም ሙላቱ ፣

እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገምሁሌም ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ ፣ ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ ፣ ለትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ ፣ ለቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል።

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን ለአዘጋጅ መምህራን ከዚህ በላይ ስራ የለም በማለት ፍቃድ በመስጠትና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችን እናቀርባለን።

# ማውጫ


ይዘት ገፅ

መግቢያ ........ ii

**ምዕራፍ አንድ ........ 1**

ጤና ........ 1

**ምዕራፍ ሁለት ........ 13**

ጉርብትና ........ 13

**ምዕራፍ ሶስት ........ 25**

ተረት ........ 25

**ምዕራፍ አራት ........ 36**

የጊዜ አጠቃቀም ........ 36

**ምዕራፍ አምስት ........ 47**

መጓጓዣ ........ 47

**ምዕራፍ ስድስት ........ 59**

ስነ ምግባር ........ 59

**ምዕራፍ ሰባት ........ 69**

ግብርና ........ 69

**ምዕራፍ ስምንት ........ 82**

ሥራ ........ 82

**ምዕራፍ ዘጠኝ ........ 96**

ባህል ........ 96

**ምዕራፍ አስር ........ 109**

ገበያ ........ 109

የቃላት ፍቺ ........ 121

ዋቢ ጽሑፎች ........ 122

የፊደል ገበታ ........ 124

የኢትዮጵያ ቁጥሮች ........ 126

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የሶስተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ በመጀመሪያ ቋንቋነት ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው። በዚህ መጽሐፍ የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ በብቃት እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀ የመጀመሪያ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት አካል ነው።

መጽሐፉ ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው ተማሪዎች ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ እንዴት እንደሚማሩ ማለማመድ ላይ የተመሰረተ ነው። ይህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት እና መርሃ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆችንም አካቷል።

፩. ተማሪዎች ስዕሎችን በመመልከት ተረቶችን ወይም ታሪኮችን ከማዳመጣች በፊት ከቀደመ እውቀታቸው በመነሳት በመተንበይ የማዳመጥና የመናገር ክሂላቸውን ያዳብራሉ።

፪. ተማሪዎች የሚነበብላቸውን ታሪክ ወይንም ምንባብ በሚገባ በማዳመጥ ያዳመጡትን ታሪክ ወይም ምንባብ በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በግልፅ ቋንቋ መናገርና መፃፍ ይጠበቅባቸዋል። ይህንንም ለማድረግ ይችሉ ዘንድ ተከታታይ የመናገርና የመፃፍ ተደጋጋሚ ልምምድ ማድረግ አለባቸው።

፫. ተማሪዎች ባዳመጡትና ባነበቡት ጽሑፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላት የሚወክላቸውን ፍች በመፃፍ በተገቢው የቃላት አሰዳደር ስርዓት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን ይማራሉ።

፬. ተማሪዎች በተለመዱና በአዳዲስ ቃላት የተመሰረቱ አረፍተ ነገሮችን ማንበብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

፭. ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የአዳዲስ ቃላትን ፍች አብረው መማር አለባቸው፡፡ በዚህም የሚያደምጡትንና የሚያነቡትን ሃሳብ ይረዳሉ፡፡ የቃላት እውቀታቸውንም በማሳደግ በንግግርና በጽሑፍ ሃሳባቸውን በአግባቡ ይገልፃሉ፡፡

፮. ተማሪዎች የተለያዩ ተረቶችን ወይም ታሪኮችን እንዲሁም ሌሎች ጽሑፎችን አንብበው መረዳት ይችሉ ዘንድ የአንብቦ መረዳት ተግባራትን በተደጋጋሚ በመስራት ማዳበር ይጠበቅባቸዋል፡፡

## ምክር ለወላጆች

ውድ የተማሪ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ልጆቻችን የቋንቋ ትምህርቱን በአግባቡ ይገነዘቡ ዘንድ የመምህራን እና የእርስዎ ጥምር እገዛ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ከግንዛቤ በማስገባት በቤትዎ ውስጥ ልጆችዎን ያግዙ፡፡

፩. ለልጆችዎ የተለያየ ታሪኮችን፣ ተረቶችን...ይንገሯቸው /ያንብቡላቸው፡፡
፪. ለልጆችዎ የነገሯቸውን/ ያነበቡላቸውን ታሪክ/ ተረት ልጆችዎ መልሰው እንዲተርኩ/ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
፫. በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ምንባቦችና ተግባራት በየጊዜው እየተከታተሉ ያሰሯቸው፡፡
፬. ልጆችዎ በራሳቸው ተነሳሽነት የተለያዩ ጽሑፎችን እንዲያዳምጡ፣ እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡና እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
፭. ልጆችዎ መምህራቸው በቤታቸው ተዘጋጅተው በመምጣት በተግባር እንዲያሳዩ የሚሰጧቸውን ለተግባራዊ ክንውን መተግበሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶች በማሟላት የወላጅነት ግዴታዎን ይወጡ፡፡

አማርኛ

፫ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አንድ
# ጤና

የምዕራፉ አላማዎች፣


ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች :-

- በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ዘገባ በቃል ታቀርባላችሁ፡፡
- የተሰጣችሁን ምንባብ በትክክለኛው አገላለፅ ታነባላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፥- ማዳመጥና መናገር

## የጥርስ ንፅህና አጠባበቅ





**የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ከስዕሉ ምን ተረዳችሁ?
2. የጥርስ ንፅህና አጠባበቅ ምንድን ነው?
3. አንድ ሰው በቀን ውስጥ ቢያንስ ስንት ጊዜ ጥርሱን መቦረሽ አለበት?

**ተግባር አንድ፥- አዳምጦ መረዳት**

**ሀ. በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ቀደም ሲል በአዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ የተጠቀሱት ስሞች ማንና ማን ናቸው?
2. ተማሪዎቹ የሚኖሩበት ከተማ የት ነው?
3. ተማሪዎቹ ስንተኛ ክፍል ናቸው?
4. የአዳመጣችሁት ምንባብ ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ምንድን ነው?

## ለ. ከላይ በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ሀሳባችሁን በፅሁፍ ግለፁ።

1. የጽሑፉ ዋና ሃሳብ ምንድን ነው?

2. አቤል የጥርስ ንፅህናውን ከመጠበቅ አኳያ ማድረግ የነበረበትን ተግባራት በጽሑፍ ግለፁ።

ተግባር ሁለት፡-ቃላት

## ሀ. ከዚህ በታች ለተሰጡት ቃላት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ተመሳሳይ ፍቻቸውን ፃፉ።

ምሳሌ፡- ሄደ = ተጓዘ

1. ቦረሸ
2. ተደጋጋሚ
3. በጠና
4. ጓደኛ
5. ወላጅ

## ለ. ከዚህ በታች ለተሰጡት ቃላት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ተቃራኒ ፍቻቸውን ፃፉ።

ምሳሌ፡- ሄደ = መጣ

1. ጎበዝ
2. ታመመ
3. ንፁህ
4. ጠዋት
5. ሴት

**ተግባር ሶስት፡ - መጻፍ**

**ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡**

ምሳሌ፡- 1. ጓደኛ፡- መሀመድ የሀና ጓደኛ ነው፡፡

2. ተማሪ፡- ዘምዘም ጎበዝ ተማሪ ናት፡፡

ከላይ በቀረቡት ጓደኛ እና ተማሪ በሚሉት ቃላት ሁለት አረፍተ ነገሮችን መመስረት ተችሏል፡፡ ተማሪዎች እናንተም ከዚህ በታች

በቀረቡት ቃላት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

1. ቀን
2. ሰው
3. ክፍል
4. ጥርስ
5. ጤና ጣቢያ
6. ሐኪም
7. መከረ

**ክፍል ሁለት፡ - ንባብ**

## የአካባቢና የግል ንፅህና



**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች፡ -**

1. ስዕሉን በመመልከት የተገነዘባችሁትን ሀሳብ በቃል ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ፡፡

2. ከርዕሱ ተነስታችሁ ምንባቡ ስለምን የሚያስረዳ ይመስላችኋል?

## የአካባቢና የግል ንፅህና

ጤናማ ለመሆን የአካባቢንና የግል ንፅህናን መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ሰዎችእንዳይታመሙ አስቀድመው ጥንቃቄ ለማድረግ አካባቢያቸውንና የግል ንፅህናቸውን በሚገባ መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡የአካባቢን ንፅህና ለመጠበቅ የአካባቢው ማህበረሰብ አካባቢውን በጋራ ማፅዳት ይጠበቅበታል፡፡ በዚህም ሰዎች ማህበረሰብ ከተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ማለትም እንደ ጉንፋንና ወባ ከመሳሰሉት ሊጠበቁ ይችላሉ፡፡

**ሰዎች የአካባቢያቸውንና የግል ንፅህናቸውን ባይጠብቁ ምን የሚሆኑ ይመስላችኋል?**

በአንድ በኩል እያንዳንዱ ሰው የግል ንፅህናውን በመጠበቅ ጤንነቱን መጠበቅ ይችላል፡፡ የግል ንፅህና ሲባል ልብስን በአግባቡ ማጠብ፣ ፀጉርን አጥቦ ማበጠር፣ እጅን በሳሙና በደንብ መታጠብ፣ እግርን መታጠብ፣ የካልሲና የጫማን ንፅህና መጠበቅ ወ.ዘ.ተ ያካትታል፡፡ በሌላ በኩል ሰዎች በአካባቢና በግል ንፅህና ጉድለት ምክንያት ሲታመሙ ፈጥነው ወደ ሐኪም ቤት መሄድ አለባቸው፡፡ ሐኪም ቤት ሄደው በሽታቸው ከተገኘ በኂላ የሚሰጣቸውን መድሃኒት በአግባቡ መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ሰዎች የአካባቢንና የግል ንፅህናን መጠበቅና ሲታመሙ መታከም በጤና ለመኖር ያስችላቸዋል፡፡

### ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

### ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

1. ጤናማ ለመሆን ምን ማድረግ ያስፈልጋል ?
2. ሰዎች ወደ ሃኪም ቤት የሚሄዱት ለምንድን ነው ?
3. አንድ ሰው ሲታመም ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ ?
4. የአካባቢውንና የግል ንፅህናውን የማይጠብቅ ሰው ምን ሊገጥመው ይችላል?

5. አንድ ሰው ከሐኪም ቤት የሚሰጠውን መድሃኒት በአግባቡ መውሰድ ያለበት ለምንድን ነው?

**ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሑፍ ሃሳባችሁን አስፍሩ።**

1. የምንባቡን ዋና ሃሳብ በአጭሩስ ግለፁ፡፡
2. የግልና የአካባቢ ንፅህናን አንድነትና ልዩነት በጽሑፍ አብራሩ፡፡
3. የግል ንፅህናችንን በሚገባ እየጠበቅን የአካባቢያችንን ንፅህና ባንጠብቅ ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?

**ሐ. በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ከሰንጠረዡ ውስጥ ተስማሚ ቃላትን በመምረጥ አሟልታችሁ ፃፉ።**

| | | |
|---|---|---|
| ሐኪም ቤት | ሰዎች | የአካባቢውን ንፅህና |
| መድሃኒት | የግል ንፅህና | በጤና |

1. ____________________ለመኖር የአካባቢንና የግል ንፅህናን መጠበቅ ይኖርብናል፡፡
2. ሰዎች ከሐኪም ቤት የሚሰጣቸውን______________በአግባቡ መውሰድ አለባቸው፡፡
3. _______________እንዳይታመሙ አስቀድመው የአካባቢያቸውንና የግል ንፅህናቸውን መጠበቅ አለባቸው፡፡
4. እያንዳንዱ ሰው የራሱን_________________መጠበቅ አለበት፡፡
5. ህብረተሰቡ በጋራ በመሆን_________________መጠበቅ ይችላል፡፡

**ተግባር ሁለት፡- አቀላጥፎ ማንበብ**

**ሀ. ተማሪዎች ከላይ <<የአካባቢና የግል ንፅህና>> በሚል የቀረበውን ምንባብ እንደገና ተራ በተራ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡**

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

**ተግባር አንድ፡- የቃላት ፍቺ**

**ሀ. በ <<ሀ>> ስር ለተዘረዘሩት ቃላት ከ <<ለ>> ስር ተመሳሳይ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| 1. መጠቃት | ሀ. በአስቸኳይ |
| 2. ተላላፊ | ለ. መጋለጥ |
| 3. በፍጥነት | ሐ. ተዛማች |
| 4. ሐኪም ቤት | መ. ማፅዳት |
| 5. ማጠብ | ሠ. የሕክምና ተቋም |

**ለ. በ<<ሀ>> ስር ለተዘረዘሩት ከ<<ለ>> ስር ተቃራኒያቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| 1. ማህበረሰብ | ሀ. በተናጠል |
| 2. በጋራ | ለ. ቆሻሻ |
| 3. በሽተኛ | ሐ. ግለሰብ |
| 4. ንፁህ | መ. በኋላ |
| 5. በቅድሚያ | ሠ. ጤነኛ |

**ሐ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ አውዳዊ ፍች በጽሑፍ መልሱ።**

ምሳሌ፡- ሀ. በአካባቢና በግል ንፅህና ጉድለት ምክንያት ሲታመሙ ፈጥነው ወደ ሐኪም ቤት መሄድ አለባቸው፡፡

መልስ፡- ፈጥነው የሚለው ቃል በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ያለው አውዳዊ ፍች ቶሎ የሚል ይሆናል፡፡
ለ. ጥንቃቄ በማድረግ በሽታን መከላከል ይቻላል፡፡

መልስ፡- መከላከል የሚለው ቃል በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ያለው አውዳዊ ፍቺ መቆጣጠር የሚል ይሆናል፡፡

1. ህፃናት የተመጣጠነ ምግብ <u>መመገብ</u> አለባቸው፡፡

2. በወባ በሽታ <u>የተያዘ</u> ሰው ያንቀጠቅጠዋል፡፡

3. ወ/ሮ ንግስት ህመሟ <u>ጠናባት</u>፡፡

4. ካሊድ ጠዋት ጠዋት <u>ሁልጊዜ</u> ፀጉሩን ይታጠባል፡፡

5. ሂክማ ለቤት ቁሳቁስ መግዣ <u>ገንዘብ</u> ወጭ አደረገች፡፡

**መ. ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉትን ቃላት ባለሶስት ወይም ባለ አራት ሆሄ መሆናቸውን የ √ ምልክት በመጠቀም አመልክቱ።**

| ተ.ቁ | የተሰጡ ቃላት | ባለሶስት ሆሄ ቃላት | ባለአራት ሆሄ ቃላት |
|---|---|---|---|
| 1 | ለበሰ | √ | |
| 2 | ሰበሰበ | | √ |
| 3 | ከበረ | | |
| 4 | ደብተር | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | እርሳስ | | |
| 6 | ተማሪ | | |
| 7 | ጠረጴዛ | | |
| 8 | አጠበቀ | | |

### ሠ. በምሳሌው መሰረት ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት ነጠላ ወይም ብዙ ቁጥር በማለት ለይታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-ደብተር - ነጠላ ቁጥር ተማሪዎች - ብዙ ቁጥር

1. ቤት
2. ድመቶች
3. ሴቶች
4. ደግ
5. መኪና
6. ቴሌቪዥን
7. ብርቱካኖች
8. ወንበር
9. እናቶች
10. መምህር

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ተግባር አንድ፡- መጻፍ

### ሀ. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የቀረቡትን የድርጊት ቅደም ተከተሎች እንደገና አስተካክላችሁ ፃፉ።

1. መፀዳጃ ቤት ሄዱ።
2. የደንብ ልብሳቸውን ለበሱ።
3. እጃቸውንና ፊታቸውን ታጠቡ።
4. ደብተራቸውን፣ መጽሐፋቸውን፣ እርሳስና እስክርቢቷቸውን ወደ ቦርሳቸው ከተቱ።
5. ወደ ትምህርት ቤት ሄዱ።
6. ከእንቅልፋቸው ተነሱ።
7. ቦርሳቸውን ያዙ።

ለ. የሳይንስ መምህራችሁን ወይም የትምህርት ቤታችሁን የጤና ባለሙያ ስለ ኮሮና ቫይረስ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች ጠይቃችሁ በቡድን ፅፋችሁ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

ሐ. የአካባቢና የግል ንፅህና አጠባበቅን አስመልክቶ ከቤተሰባችሁ ወይም ከጎረቤቶቻችሁ በግል ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- አያያዦች

**ማስታወሻ**

አያያዦች ቃልን ከቃል፣ ሀረግን ከሀረግና አረፍተ ነገርን ከአረፍተ ነገር ጋር የሚያያይዙ ናቸው። አያያዥ ቃላት ወይም ሀረጋት ከሚባሉት መካከል ለምሳሌ ነገር ግን፣ እንጂ፣ እና፣ ስለዚህ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ።

ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት ወይም ሀረጋት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በቡድን ሆናችሁ አስምሩባቸው።

ምሳሌ፡- ሀ. ትምህርት ቤት መሄድ እፈልጋለሁ፣ ነገር ግን ደክሞኛል።

ለ. ያሬድ ጎበዝ ተማሪ ስለሆነ ጥሩ ውጤት አስመዘገበ።

1. የፒያሳ ልጆች መልካሞች ስለሆኑ የተቸገረን ይረዳሉ።

2. ኢትዮጵያ የጀግኖች ሀገር እንጂ የሌቦች አይደለችም።

3. ሰአዳ መምህር እንጂ ሃኪም አይደለችም።

4. ፈተና ደርሷል ስለዚህ ማንበብ አለብኝ።

5. ይሳኮር መፅሐፍ ማንበብ ሲወድ ቅድስት ግን ፊልም ማየት ትመርጣለች፡፡

6. አዲስ አበባ የቱሪስት መዳረሻ ብትሆንም በቂ የመዝናኛ ስፍራዎች የሏትም፡፡

## ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም በምሳሌው መሰረት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ነገር ግን

ዳመናው ዳምኗል፣ <u>ነገር ግን</u> ዝናብ አልጣላም፡፡

1. ስለሆነም
2. ይሁን እንጂ
3. ነገር ግን
4. ቢሆንም
5. ስለዚህ
6. እና

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የግልና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅን አስመልክቶ በሬዲዮና ቴሌቪዥን የሚተላለፉ መረጃዎችን አዳምጣችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ፡፡

2. የግልና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅን አስመልክቶ የተፃፉ ምንባቦችን ፈልጋችሁ በማምጣት በክፍል ውስጥ አቀላጥፋችሁ አንብቡ፡፡

3. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ተጋላጭ | መ. መዛባት |
| ለ. ጥሞና | ሠ. መጠበቅ |
| ሐ. መትጋት | ረ. ፈጠራ |

4. በግልና አካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ጉድለት ሊከሰቱ የሚችሉ የጤና እክሎችን በአምስት አረፍተ ነገሮች ፃፉ፡፡

5. በሚከተሉት አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ስለሆነም | ሐ. ቢሆንም |
| ለ. እንጂ | መ. ስለዚህ |

አማርኛ

፫ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሁለት
# ጉርብትና

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ተመሳሳይ ታሪክ አዳምጣችሁ በድጋሜ ትናገራላችሁ፡፡
- አጫጭር ምንባቦችን አቀላጥፋችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ለቃላት ተቃራኒና ተመሳሳይ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ትፅፋላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፤- ማዳመጥና መናገር

## ጉርብትናና ጠቀሜታው





**የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ስዕሉን ተመልክታችሁ የተገነዘባችሁትን ሃሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ::
2. ርዕሱን ተመልክታችሁ ስለምን እንደሚገልፅ ተናገሩ::
3. መልካም ጉርብትና ማለት ምን ማለት ነው?

**ተግባር አንድ፤- አዳምጦ መረዳት**

**ሀ. በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. በአዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ በመልካም ጉርብትናቸው የተጠቀሱት እነማን ናቸው?
2. የተጣላን የሚያስታርቁትና የተቸገረን የሚረዱት እነማን ናቸው?
3. አቶ አምሃ ሴት ልጃቸውን ሲድሩ ጎረቤቶቻቸው ምን አደረጉላቸው?
4. ወይዘሮ ሃያትና አቶ አምሃ በጎረቤቶቻቸው ደስተኛ የሆኑት ለምንድን ነው?

5. የሰርግ ስነ-ስርዓቱን ከስራ ጀምሮ እስከ ፍፃሜ ያደመቁት እነማን ናቸው?

6. የሰው ልጆች መልካም ጎረቤት ባይኖራቸው ምን ይሆናሉ?

**ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች አንብባችሁ የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ ''እውነት'' ስህተት ከሆነ ደግሞ ''ሀሰት'' በማለት በቃል መልሱ። ምክንያታችሁንም ግለፁ።**

1. በመልካም ጉርብትና መኖር የሰዎችን ማህበራዊ ህይወት ያጠነክራል፡፡

2. በቤታቸው እንግዳ ተቀባይ ናቸው የተባሉት ወይዘሮ ሃያት ናቸው፡፡

3. ከዩኒቨርሲቲ ተመርቆ የመጣው የአቶ አምሃ ሁለተኛ ልጅ ነው፡፡

4. አቶ አምሃና ወይዘሮ ሃያት የሚኖሩት መገናኛ አካባቢ ነው፡፡

5. በመልካም ጉርብትና የሚኖሩ ሰዎች እርስ በእርስ መደጋገፍ አለባቸው፡፡

**ሐ. ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተነጋግራችሁ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።**

1. እናንተ በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ጎረቤቶቻችሁን ጥቀሱ፡፡

2. ከጎረቤቶቻችሁ ጋር ስትኖሩ ለጎረቤቶቻችሁ ምን ምን ታደርጉላቸዋላችሁ?

3. ጎረቤቶቻችሁ ለእናንተ ምን ምን ያደርጋሉ?

4. ከአዳመጣችሁት ታሪክ ጋር የሚመሳሰል ሌላ ታሪክ ከቤተሰቦቻችሁ ጠይቃችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃላችሁ ተርኩ፡፡

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**ሀ. ከዚህ በታች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ዓረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፤ በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡**

1. ጉርብትና ለእርስ በእርስ ትስስር ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡
2. የሰርግ ስራውን በመረዳዳት እስከ ፍፃሜው አደመቁት፡፡
3. ማህበራዊ ህይወት የሚጎለብተው መልካም ጉርብትና ሲኖር ነው፡፡
4. አቶ አምሃ የተጣላን ጎረቤት በማስታረቅ ይታወቃሉ፡፡
5. ወይዘሮ ሃያት አመት በዓል ሲመጣ ለጎረቤቶቻቸው አስፈላጊውን እገዛ ሁሉ ያደርጋሉ፡፡

**ለ. ከዚህ በታች ከማዳመጥ ምንባብ ውስጥ ለወጡ ቃላት በምሳሌው መሰረት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡**

ምሳሌ፡- መልካም = ጥሩ፣ ያማረ፣ ሳቢ፣ አስደሳች ወ.ዘ.ተ.

1. መቻቻል
2. መከባበር
3. መተማመን
4. ምስጉን
5. ማድመቅ

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### <<ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት>>

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት



### <<ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት>>

ጎረቤታሞች በበዓላት ወቅት ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት በየተራ እየተጠራሩ በመገባበዝ በደስታ አብረው ያሳልፋሉ:: ተነፋፍቆ የተገናኘው ዘመድ፣ በተለያየ መንገድ ዝምድናና ወዳጅነት የፈጠረው ሁሉ በዚህ መልኩ ተሰብስቦ በሳቅ በጨዋታ ያሳልፋል:: የአብሮነት፣ የአንድነትና የማህበራዊ ግንኙነቱ ማሳያ በሆነው በዓል ወቅት ብዙዎች ደስታቸውን ያጣጥማሉ:: ሁሉም እንደየ እምነቱ በዓሉን ቢያከብርም ክርስቲያኑ ሙስሊም ጎረቤቱን፣ ሙስሊሙም እንዲሁ ክርስቲያን ጎረቤቱን ጠርቶ ያለውን በወንድማማችነት መንፈስ ተካፍለው በደስታ በዓሉን ያከብራሉ:: ሰርግም ሲደግሱ እንዲሁ አይለያዩም:: ስጦታቸውን ይዘው በመሄድ ይታደማሉ::

**ጎረቤታሞች ዓመት በዓልን በጋራ ከማሳለፍ በተጨማሪ በምን በምን ሊረዳዱ ይችላሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?**

እንዲህ በበዓል ወቅት ትስስሩ ይጠነክራል ለማለት እንጂ ሰዎች በጉርብትና አብረው ሲኖሩ አንዳቸው ለሌላኛው የሚያሳዩት ፍቅርና መተሳሰብ ጠንካራ ነው:: ጩኸት እንኳን ሲሰማ ጎረቤት ቀድሞ ይወጣል:: ፀብም ከሆነ መሃል ገብቶ ይገላግላል:: ድረሱልኝ ብሎም ከተጣራ ሰምቶ የሚተኛ ጎረቤት የለም:: ከነአባባሉም ‹‹ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት ይሻላል›› ይባላል:: መተሳሰቡ ከዚህም አልፎ ልጅን በጉዲፈቻ ወስዶ እንደራስ ልጅ አድርጎ በማሳደግ ይታወቃል:: እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለብን አንድ ሰው ልጅ በጉዲፈቻ ለማሳደግ ሲወስድ ዘር ጠይቆ ወይም ቆጥሮ አይደለም:: በደም ከማይተሳሰረው ሰው ጋር በልጁ አማካኝነት ዝምድናውን ለማጠናከር ሲል የሚያደርገው ተግባር ነው::

አዲስ ዘመን ግንቦት 1 ቀን 2013 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዌብ ሳይት ላይ ለማስተማሪያነት እንዲመች ተደርጎ የተወሰደ::

## ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. ጎረቤታሞች እየተጠራሩ የሚገባበዙት በምን ወቅት ነው?
2. በምንባቡ መሰረት የአብሮነትና የማህበራዊ ግንኙነት ማሳያ የሆነው ምንድን ነው?
3. በበዓላት ወቅት በወንድማማችነት መንፈስ ተካፍለው ያከብራሉ የተባሉት እነማን ናቸው?
4. ጩኸት እንኳ ሲሰማ ቀድሞ ይደርሳል የተባለው ማን ነው?
5. ‹‹ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት›› ከሚለው ምንባብ ምን ተረዳችሁ? ተራ በተራ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ::

**ለ. ከዚህ ቀጥሎ ምንባቡን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዳቸው ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል/ሆሄ ምረጡ፡፡**

1. ጎረቤታሞች በበዓላት ወቅት በምን በምን ጊዜ ሊጠራሩ ይችላሉ?

   ሀ. በቁርስ ለ. በምሳ ሐ. በእራት መ. በሁሉም

2. ልጅን እንደራስ ልጅ ወስዶ ማሳደግ ምን ይባላል?

   ሀ.ጉዲፈቻ ለ.አምቻ ሐ.ጋብቻ መ.የአብራክ ክፋይ

3. በደም ከማይተሳሰሩት ጋር ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?

   ሀ. ዘመዳሞች ለ. ዝምድና የሌላቸው

   ሐ. ወንድማማቾች መ. እህትማማቾች

4. ከሚከተሉት ውስጥ ጠንካራ ማህበራዊነት እንዲኖር የሚያስችለው የቱ ነው?

   ሀ. ፍቅር ለ. መከባበር ሐ. መተሳሰብ መ. ሁሉም

**ሐ. ከዚህ በታች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ወይም ሀረጋት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡**

1. ተነፋፍቆ የተገናኘ ቤተ ዘመድ ሁሉ ተሰባስቦ በሳቅ <u>በጨዋታ</u> በዓልን ያሳልፋል፡፡

2. <u>የአንድነት</u>ና የማህበራዊ ግንኙነት ማሳያ በሆነው በዓል ወቅት ብዙዎች ደስታቸውን <u>ያጣጥማሉ</u>፡፡

3. በሰርግ ድግስ ወቅት <u>ታዳሚዎች</u> ስጦታ ይዘው ይሄዳሉ፡፡

4. እዚህ ላይ መዘንጋት <u>የሌለብን</u> <u>አ</u>ንድ ሰው <u>በጉዲፈቻ</u> ልጅ ሲወስድ ዘር ጠይቆ አይደለም፡፡

## ተግባር ሁለት ፡- አቀላጥፎ ማንበብ

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ፣ መምህራችሁ በሚሰጣችሁ መመሪያ መሰረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።**

### ፌኔትና ያዕቆብ

ፌኔትና ያዕቆብ የአዲሱ ገበያ አካባቢ ልጆች ናቸው፡፡ ፌኔት በትምህርቷ በጣም ጎበዝ በመሆኗ የቤት ስራዋን በአግባቡ ሰርታ ትመጣለች፡፡ በዚህም የተነሳ መምህሮቿ በጣም ይወዷታል፡፡ ያዕቆብ ደግሞ ስለማያጠናና የቤት ስራውንም በአግባቡ ስለማይሰራ መምህራኑ ሁልጊዜ ይቆጡታል፡፡

ፌኔት ይህንን ተመልክታ ያዕቆብን ‹‹አንተ ለምን አታጠናም? የቤት ስራህንስ ለምን ሰርተህ አትመጣም?›› ስትል ጠየቀችው፡፡ ያዕቆብም ‹‹ከእንግዲህ ወዲህ ጊዜየን በአግባቡ በመጠቀም የቤት ስራየንም ሰርቼ እመጣለሁ›› በማለት የፌኔትን ምክር ተቀብሎ በጋራ ማጥናት ጀመሩ፤ የቤት ስራቸውንም አብረው መስራት ቀጠሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ያዕቆብ በትምህርቱ ከቀን ቀን በከፍተኛ ሁኔታ እየተሻሻለ መጣ፣ በዚህም ምክንያት ሁለቱም ጓደኛሞች በሰፈሩም ሆነ በትምህርት ቤቱ የታወቁ አርዓያ ተማሪዎች መሆን ቻሉ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

**ሀ. ለሚከተሉት ቃላት በ<<ሀ>> ረድፍ ላሉት ከ<<ለ>> ረድፍ ተመሳሳይ ፍች በመምረጥ አዛምዱ።**

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| 1. መስተጋብር | ሀ. ደግ/መልካም |
| 2. ቅን | ለ. አታላይ/አጭበርባሪ |
| 3. ሸንጋይ | ሐ. ግንኙነት/ትስስር |

4. ተወዳጅ መ. ተዛመደ/ተፋቀረ
5. አሰናዳ ሠ. ሀሴት/ፈንጠዝያ
6. ደስታ ረ. አዘጋጀ/ሰራ

## ለ. ለሚከተሉት ቃላት በ<<ሀ>> ረድፍ ላሉት ከ<<ለ>> ረድፍ ተቃራኒ ፍቺ በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሰጠ | ሀ. ራስጌ |
| 2. ባህላዊ | ለ. ከለከለ |
| 3. ግርጌ | ሐ. ሰበሰበ |
| 4. ፍቅር | መ. ዘመናዊ |
| 5. በተነ | ሠ. መራራ |
| 6. ጣፋጭ | ረ. ጥላቻ |

## ሐ. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ውስብስብ ሆሄያት ለይታችሁ አውጡ።

| | |
|---|---|
| ምሳሌ፡- ተጓዘ | ጓ |
| ተንኳኳ | ኳ |
| ላሟ | ሟ |

| ተ.ቁ | ቃላት | |
|---|---|---|
| 1 | ሯጭ | |
| 2 | ፏፏቴ | |
| 3 | በኋላ | |
| 4 | ታንኳ | |
| 5 | ቧንቧ | |

### መ. የሚከተሉትን ውስብስብ ሆሄያት በመጠቀም ቃላትን መስርቱ።

ምሳሌ፡- ሏ = ልብሏ

1. ጧ
2. ቋ
3. ሿ
4. ቷ
5. ሷ

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ማስታወሻ

#### ስርዓተ ነጥቦች

በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የተለያዩ ስርዓተ ነጥቦች አሉ። እነዚህን ስርዓተነጥቦች ጥቅም ላይ የምናውላቸው በጽሑፍ ወቅት ሲሆን ጽሑፍ ለአንባቢ ግልፅ የሆነ መልዕክትን ለማስተላለፍ ያግዛሉ። በጽሑፎች ውስጥ ተዘውትረው ጥቅም ላይ የሚውሉት ስርዓተ ነጥቦች የሚከተሉትን ይመስላሉ።

1. **ጥያቄ ምልክት** (?) ይህ ስርዓተ ነጥብ ጥያቄያዊ አረፍተ ነገሮችን ለማቅረብ ያገለግላል።
   ምሳሌ፡- መቼ መጣህ?

2. **ነጠላ ሰረዝ** (፣) ይህ የስርዓተ ነጥብ ምልክት የሚያገለግለው ተመሳሳይነት ያላቸውን ተከታታይ ነገሮች በምንዘረዝርበት ጊዜ በመካከላቸው ለመለያነት በመግባት ያገለግላል።
   ምሳሌ፡- በፀሎት ለትምህርት የሚያስፈልጓትን እንደ ኬን፣ ብሬል፣ መጽሐፍና ደብተር ገዛች።

3. **ቃለ አጋኖ** (!) ይህ የስርዓተ ነጥብ ምልክት ለሰዎች ማስጠንቀቂያ በምንናገርበት ጊዜ ወይም አድናቆታችን በምንገልፅበት ጊዜ በጽሑፍ ውስጥ የምንጠቀምበት ነው፡፡
ምሳሌ፡- ተጠንቀቁ! ዋው! እንዴት ያለ ጎበዝ ልጅ ነው፡፡

4. **ትዕምርተ ጥቅስ** (‹‹ ››) ይህ የስርዓተ ነጥብ ምልክት የሚያገለግለው ሰዎች የፃፉትን ወይም የተናገሩትን ከራሳችን ሀሳብ በጽሑፍ ውስጥ ለይተን የምናመለክትበት ነው፡፡

ምሳሌ፡- መምህሩ ‹‹በርትታችሁ አጥኑ›› ሲሉ መከሩን፡፡

## ሀ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የገቡትን ስርዓተ ነጥቦች ለይታችሁ ፃፉ፡፡

1. መቼ ትመጫለሽ?
2. እሱ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡
3. ዋው! እንዴት ታምራለች፡፡
4. ታምራት የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡
5. እሰይ! በጉጉት የሚጠበቀው የህዳሴው ግድባችን ሊጠናቀቅ ነው፡፡

## ለ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በተገቢው ስርዓተ ነጥብ አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

1. ይገርማል በጣም ግዙፍ ነው
2. ሰርተን መለወጥ የምንችልባት ውብ ሀገር አለችን
3. ባቄላ አተር አኩሪ አተርና ሽምብራ የጥራጥሬ እህሎች ናቸው
4. የአማርኛ መምህራችን በርትቶ ያጠና ተማሪ ጥሩ ውጤት ያመጣል እያሉ በተደጋጋሚ ይመክሩናል
5. እጅን በተደጋጋሚ በሳሙና መታጠብ ኮሮና ቫይረስን ለመከላከል ከሚያስችሉ መንገዶች አንዱ ነው

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትዕዛዙን መሰረት በማድረግ መልሳችሁን ስጡ፡፡**

1. ማህበራዊ ግንኙነትን ሊያጎለብቱ የሚችሉ ጉዳዮችን ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን አድምጣችሁ በመፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
2. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍች ስጡ፡፡

   ሀ. መወዳጀት

   ለ. መለገስ

   ሐ. አብሮነት

   መ. ታጋሽነት
3. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተጓደሉትን የስርዓተ ነጥብ ምልክቶች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

   ሀ. የሒሳብ መምህራችን የቤት ስራችሁን በአግባቡ ስሩ አሉ

   ለ. ደብተር እርሳስ እስክብሪቶና መፅሐፍ የትምህርት መሳሪዎች ናቸው

   ሐ. የአንድነት ፓርክ ሊጎበኝ የሚገባው የመዝናኛ ስፍራ ነው

   መ. አቤል የአካል ጉዳተኝነቱ ሳያግደው ምርጥ የፈጠራ ውጤት ሰርቶ አቀረበ

አማርኛ

፫ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሦስት


## ተረት

**የምዕራፉ አላማዎች፣ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ያዳመጣችሁትን ተረት ትተርካላችሁ፡፡
- በተረት ውስጥ ያሉትን ዋና ገፀ ባህሪያት ትናገራላችሁ፡፡
- ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ጠብቃችሁ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ አጭር ተረት ታነባላችሁ፡፡
- የታሪኩን ዋና ሃሳብ ትፅፋላችሁ፡፡
- በምንባቡ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት ፍች ትገምታላችሁ፡፡
- በተለያዩ ጽሑፎች ውስጥ ያሉ ስሞችን ትለያላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

### ሰማዕቷ እናት



### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን ስትመለከቱ ምን የሚል ተረት አስታወሳችሁ?
2. ‹‹ሰማዕቷ እናት›› የሚለው ተረት ስለምን የሚነግረን ይመስላችኋል?

### ተግባር አንድ፦ አዳምጦ መረዳት

**ሀ. በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ልጁ በድርጊቱ የተፀፀተው በምን ምክንያት ነው?
2. እናት የገዛ ልጇ ‹‹ሰራተኛዬ ናት›› እያለ ሲያስተዋውቃት ቅር ያልተሰኘችው ለምንድን ነው?
3. በተረቱ ውስጥ የተጠቀሱት ዋና ዋና ባለታሪኮች (ገፀ ባህሪያት) እነማን ናቸው?

4. በተረቱ ውስጥ ‹‹እናት ጥራ ግራ ልጇን ትመግበው ነበር›› ይላል። ልጅን ተንከባክቦ ማሳደግና መመገብ የእናት ሀላፊነት ብቻ ይመስላችኋል? ለምን? ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተነጋገሩበትና ለመምህራችሁ ተናገሩ።

5. ልጁ ስለእናቱ እውነተኛ ታሪክ ቢያውቅ ይህን የሚያደርግ ይመስላችኋል?

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መምህራችሁ በሚያደራጇችሁ ቡድን ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሀሳብ በጽሑፍ አስፍሩ።**

1. በተረቱ ውስጥ ‹‹የእሷ ውበት ከእኔ ላይ ነው፤ የእኔ ጠባሳ ደግሞ እሷ ላይ ነው›› የሚለው ሀሳብ የሚያስተላልፈውን መልዕክት በፅሁፍ መልሱ።

2. ‹‹ሰማዕቷ እናት›› የሚለው ተረት የሚያስተላልፈውን ፍሬ ሀሳብ በአራት አረፍተ ነገር በፅሁፍ ግለፁ።

3. ከዚህ ተረት ጋር የሚዛመድ እውነተኛ ታሪክ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? የምታውቁትን በፅሁፍ አስፍሩ።

ተግባር ሁለት ፡- ቃላት

**ሀ. ከላይ ከአዳመጣችሁት ተረት ውስጥ ለወጡት አዳዲስ ቃላትና ሀረጋት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ቀጥተኛ ፍች ስጡ።**

ምሳሌ፡- ተመለከተ = አየ

ባልንጀራ = ጓደኛ

1. አወጋችው
2. ሰማዕቷ
3. ጠቅልዬ
4. ጥራ ግራ
5. ደፋ ቀና
6. መተኪያ የሌለው

**ለ. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ።**

1. መስራት
2. መልከኛ
3. አንድ ለእናቱ
4. ክፉኛ ተጎዳሁ
5. ይገኙ ቀረሁ
6. ቅር መሰኘት

**ሐ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ከሰጣችሁ በኋላ በፍችው ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ።**

ምሳሌ፡- መከወን = መፈፀም

ስራችንን በጊዜ መፈፀም ተገቢ ነው።

1. ተቃጠለ
2. ተበላሸ
3. ሳተርፍህ
4. የተከበረ
5. መፀፀት

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር አንድ፡- እንቆቅልሽ

**ሀ. ከዚህ በታች በቡድን በመሆን የምትጠያየቁት እንቆቅልሽ ቀርቦላችኋል። መምህራችሁ በሚያደራጇችሁ ቡድን መሰረት እንቆቅልሹን ተጠያየቁ። እንቆቅልሹን ስትጠያየቁ አንዱ ጠያቂ ሌላው መላሽ ሁኑ። መላሽ የነበረው ደግሞ በተራው ጠያቂ ይሁን። የእንቆቅልሽ ሂደቱን ጠብቃችሁ ተጠያየቁ።**

ምሳሌ፡-

ጠያቂ = እንቆቅልሽ/ህ

መላሽ = ምን አውቅልሽ/ህ

ጠያቂ = ወተቷ ይጠጣ ስጋዋ አትበላ መላሽ = እናት

1. በልቶ የማይጠግብ ያገኘውን የሚውጥ

2. ትንሽ ምላጭ ሀገር ትላጭ

3. እሷ ጥቁር ልጆቿ ነጫጭ

4. አፍ የላት ትናገራለች እግር የላት ትሮጣለች

5. ሲሄድ ሺህ ገዳይ ሲመለስ ሺህ ገዳይ

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### ዛፎች



### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን ተመልከቱና የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ::

2. ‹‹ዛፎች›› የሚለውን ርዕስ ስታነቡ ምን አስታወሳችሁ?

## ዛፎች

ከዕለታት አንድ ቀን በዓለም ዙሪያ ያሉ ዛፎች ተሰባስበው ስለችግሮቻቸው ይወያዩ ነበር፡፡

ከመሃከላቸውም አንዱ ዛፍ እንዲህ አለ ‹‹የእኛ ትልቁ ችግር የደን መመንጠር ነው፡፡ይህም ድርጊት የሚፈጸምብን መጥረቢያ በተባለ መሳሪያ ነው፡፡ ስለዚህ ጠላታችን የሆነውን መጥረቢያን ማጥፋት አለብን›› አለ፡፡

ብዙዎቹም በዚህ ሃሳብ ዙሪያ አስተያየት በመስጠት ‹‹መጥረቢያ ነው የሁልጊዜ የስቃያችን ምንጭ ይቆርጠንና ቢያሻው ለማገዶ አሊያም ለቤት እቃ መስሪያ፤ አረ ምኑ ቅጡ! ስለዚህ አንድ መላ ፈልገን ይህንን ጠላታችንን ማጥፋት አለብን›› ብለው መከሩ፡፡

### ቀጥሎ ዛፎቹ ምን የሚሉ ይመስላችኋል?

አንድ ባህር ዛፍም እጁን አውጥቶ ‹‹ጠላታችን ግን መጥረቢያ አይመስለኝም›› አለ፡፡

በዚህን ጊዜ ሁሉም ዛፎች ወደርሱ ዞረው ‹‹እንዴ! ምን ማለትህ ነው? እሱ ካልሆነ ታዲያ ማን ሊሆን ይችላል?›› ብለው ጮሁበት፡፡ ባህር ዛፉም ንግግሩን እንዲህ ሲል ቀጠለ ‹‹አያችሁ እኔ ከልቤ ነው የምላችሁ ጠላታችን መጥረቢያ አይደለም እኛው ራሳችን ነን፡፡ ሁላችንም መጣመም ትተን ቀጥ ብለን ብናድግ ኖሮ መጥረቢያ እጀታ አይኖረውም፤ እኛም ከመቆረጥ እንድን ነበር፡፡

ስለዚህ ከዚህ በኋላ ሁላችንም ሳንጣመም ቀጥ ብለን በማደግ መጥረቢያውን እጀታ ማሳጣት አለብን፡፡›› በዚህ ጊዜ ሁሉም ዛፎች አጨበጨቡለት፡፡

አብርሃም እንደሻው፣ ኢትዮጲስ ቁጥር ሁለት፣ (ዓመተ ምህረቱ ያልታወቀ) ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የቀረበ

### ተግባር አንድ፦ አንብቦ መረዳት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡**

1. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በቃል ተናገሩ፡፡
2. ደኖች የሚመነጠሩት በምንድን ነው?
3. በአለም ዙሪያ ያሉት ዛፎች ተሰብስበው የተወያዩት ምን ችግር ገጥሟቸው ነው?
4. የዛፎች መቆረጥ ችግሩ የዛፎች ነው ወይስ የሰው ልጅ ይመስላችኋል? ተወያዩበት፡፡
5. ሁላችንም መጣመም ትተን ቀጥ ብለን ብናድግ ኖሮ መጥረቢያ እጀታ አይኖረውም ሲል ምን ማለት ፈልጎ ይመስላችኋል?

**ለ. በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. በምንባቡ ውስጥ ዛፎቹ ምንን ወክለው የቀረቡ ገፀ ባህሪያት ናቸው?
2. ባህር ዛፍ ጠላታችን መጥረቢያ አይደለም እኛው እራሳችን ነን ያለው ለምንድን ነው? አንድ ነገር እንዴት ለራሱ ጠላት ይሆናል? በቡድን ተወያዩበትና የደረሳችሁበትን ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡
3. ምንባቡን እንደገና አንድ ጊዜ በፅሞና ደግማችሁ በማንበብ የተረዳችሁትን የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ በሶስት አረፍተ ነገሮች ፃፉ፡፡

**ተግባር ሁለት ፡- ቃላት**

**ቀጥሎ በቀረቡት በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ።**

1. ተክል ማደግ እንዲችል ውሃና አየር ያስፈልገዋል።
2. የደኖች መመንጠር ለአንድ ሀገር እድገት ፀር ነው።
3. ገንዘብን ያለ አግባብ ማጥፋት ለድህነት ያጋልጣል።
4. የሰው ልጅ ህይወት በትራፊክ አደጋ እንዳይቀጠፍ መላ ሊበጅለት ይገባል።
5. ተማሪዎቹ በትምህርት ቤታቸው ንፅህና አጠባበቅ ላይ ተገናኝተው መከሩ።
6. መጣመም ትተን ቀጥ ብለን ብናድግ መጥረቢያ እጄታ አይኖረውም።

**ተግባር ሶስት፡- አቀላጥፎ ማንበብ**

**ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ትዕዛዝ**

**ጭልፊቷ**

ጭልፊቷ ጫጩት ፈለፈለችና መግባ ታቅፋ አሳደገች። ጫጩቷ አድጋ ክንፍ ከበቀለላት በኋላ ለመብረር ብቃት ያላት መሆኗን አረጋገጠች። ከዚያም እናቷን ‹‹እማዬ እንግዲህ ለመብረር እየተዘጋጀሁ ነው፤ ከመብረሬ በፊት ግን የምትመክሪኝ ነገር ካለ ካሁኑ ንገሪኝ›› አለቻት። እናትም ‹‹ሰዎች አንችን አይተው ጎንበስ ያሉ እንደሆነ ሰላምታ ነው ብለሽ ቀረብ ቀረብ እንዳትይላቸው። ምክንያቱም ከአንገታቸው ጎንበስ የሚሉት ድንጋይ አንስተው ክንፍሽን ሊያደቁልሽ ነው ›› በማለት መከረቻት ።

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ተግባር አንድ ፡- መጻፍ

**ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ አረፍተ ነገር በጽሑፍ መስርቱ፡፡**

ምሳሌ፡- ተረት = የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎች ተረት ይወዳሉ፡፡

1. ክንፍ
2. ጭልፊት
3. ምክር
4. በረረ
5. ብቃት

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት በጽሑፍ መልሱ፡፡**

1. የተለያዩ የተረት መፅሐፎችን ፈልጋችሁ አንብቡና ተረቱን በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡
2. ጥንድ ጥንድ በመሆን አንድ የምታውቁትን ተረት መርጣችሁ ተረቱን በራሳችሁ አገላለፅ መልሳችሁ ፃፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- ስሞችን መለየት

**ስም**

ስም የተለያዩ ነገሮች መጠሪያ ወይም ስያሜ ነው፡፡ የሰዎች፣ የቁሳቁሶች፣ የሀገሮች፣ የነገሮች፣ የቦታዎች፣ ወዘተ. መጠሪያወይም ስያሜ ስም ይባላል፡፡

ለምሳሌ፡-

የቁሳቁሶች፡- ቤት፣ መኪና፣ ቦርሳ፣ ጫማ፣ አልጋ... የሰዎች፡- ኑሪያት፣ አክመል፣ ሄርሜላ፣ አስራት... የከተሞች፡- ሀዋሳ፣ ሰመራ፣ ባህርዳር፣ ጅግጅጋ፣ አዳማ...የቦታዎች፡- መርካቶ፣ ሳሪስ፣ ሽሮ ሜዳ...

**ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተጠቀሱትን ስሞች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ለይታችሁ አውጡ።**

ምሳሌ፡-

1. አስቴር ነገ ሾላ ገበያ ትሄዳለች:: (አስቴር፣ ሾላ፣ ገበያ) እነዚህ በቅንፍ ውስጥ የቀረቡት ቃላት ስሞች ናቸው::
2. ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ትላልቅ ወንዞች መካከል አባይ፣ ባሮ፣ አዋሽ ይጠቀሳሉ:: (ኢትዮጵያ፣ ወንዞች፣ አባይ፣ ባሮ፣ አዋሽ) እነዚህ በቅንፍ ውስጥ ተለይተው የቀረቡት ቃላት ስሞች ናቸው::

1. የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎች ጎበዞች ናቸው::
2. ያሬድ ቤት፣ መኪናና ሳይክል ገዛ::
3. ጥጥ የባህል ልብስ ይሰራበታል::
4. ኮተቤ፣ ቀበናና ቤላ የካ ክፍለ ከተማ ውስጥ ይገኛሉ::
5. በግ፣ ፍየል፣ ዶሮ፣ ድመትና ውሻ የቤት እንስሳት ናቸው::

**ለ. ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን ሰሞች የሰው፣የቁሳቁስ እና የቦታ እያላችሁ በተገቢው ቦታ ምልክት አድርጉ።**

| ተ.ቁ | ስሞች | የሰወስ ሞች | የቁሳቁስ ስሞች | የቦታ ስሞች |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ጎንደር | | | √ |
| 2. | ቴሌቪዥን | | √ | |
| 3. | ፊቨን | √ | | |
| 4. | ጅማ | | | |
| 5. | ወንበር | | | |
| 6. | ሩቅያ | | | |
| 7. | ሐረር | | | |
| 8. | ይስሀቅ | | | |

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

1. አንድ የልጆች ተረት አድምጣችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተርኩላቸው፡፡
2. የተረት መፅሐፍ ፈልጋችሁ በማንበብ ባለታሪኮቹን ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
3. ለሚከተሉት ቃላት ቀጥተኛ ፍች ስጡ፡፡

    ሀ. መተረክ

    ለ. መሰባሰብ

    ሐ. መመካከር

4. እንቆቅልሽ ሲባል መልሱ ምን ሊሆን ይገባዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት
## የጊዜ አጠቃቀም

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ስለሰዓት አጠቃቀም አዳምጣችሁ ትወያያላችሁ፡፡
- ጽሑፉን አንብባችሁ መልዕክቱን ትናገራላችሁ፡፡
- በቃል እየተነገራችሁ አረፍተ ነገሮችን ትፅፋላችሁ፡፡
- የተውሶ ቃላትን ትለያላችሁ፡፡
- ግሶችን ትለያላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

### <<የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች>>



**የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ::

2. ‹‹የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች›› በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ

**ተግባር አንድ ፡- አዳምጦ መረዳት**

**ሀ. በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. በአንድ ቀን ውስጥ ስንት ሰዓታት አሉ?

2. የነገ ሀገር ተረካቢዎች የተባሉት እነማን ናቸው?

3. ከአዳመጣችሁት ምንባብ የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ::

4. ሀገራችን የምን የምን ሙያ ባለቤት የሆነ ትውልድ ያስፈልጋታል?

5. አንድ ተማሪ ጊዜውን በአግባቡ ከፋፍሎ ባይጠቀም ምን የሚሆን ይመስላችኋል?

**ተግባር ሁለት ፡- ቃላት**

**ከዚህ በታች በ<<ሀ>> ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ከ<<ለ>> ረድፍ ተመሳሳይ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ።**

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| 1. አግባብ | ሀ. ማነፅ |
| 2. መበርታት | ለ. ተገቢ |
| 3. መገንባት | ሐ. መጠንከር |
| 4. መሰረት | መ. መስክ |
| 5. ከፋፍሎ | ሠ. መገንዘብ |
| 6. መረዳት | ረ. መነሻ |
| 7. ዘርፍ | ሰ. መድቦ |

**ተግባር ሶስት ፡- ጽሕፈት**

**ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ።**

1. ሰሌዳ
2. ትውልድ
3. ህይወት
4. ልምድ
5. ብቃት

ለ. ከዚህ በታች መልሳችሁን ለቀረቡት ጥያቄዎች ትዕዛዙን መሰረት በማድረግ በፅሑፍ አስፍሩ።

1. ጊዜን በአግባቡ መጠቀም እንዴት ውጤታማ ሊያደርግ እንደሚችል በሶስት አረፍተ ነገሮች ፃፉ::

2. አንድ ተማሪ ለትምህርቱ ጠንካራ ፍላጎት ባይኖረው ምን ሊሆን ይችላል? ሀሳባችሁን በሁለት አረፍተ ነገሮች በፅሁፍ አስፍሩ::

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር አንድ፦ ምልልስ

ሀ. ተማሪዎች ከዚህ በታች የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ትዕዛዝ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን ምልልስ አድርጉ።

ምሳሌ፡-

አቤኔዘር፡- ጠዋት ስንት ስዓት ትነሻለሽ? ቬሮኒካ፡- አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል:: አንተስ?

አቤኔዘር፡- ለአንድ ሩብ ጉዳይ:: ትምህርት ቤት ስንት ሰዓት ትደርሻለሽ?


ቬሮኒካ፡- አንድ ሰዓት ተኩል:: አንተ ትቀድመኛለህ?

አቤኔዘር፡- አዎ እኔ እቀድምሻለሁ:: አንድ ሰዓት ከሩብ እደርሳለሁ:: ቤታችን ቅርብ አይደል::

## ክፍል ሶስት፣ - ንባብ

<<ናርዶስና ልዑል>>





### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. ስለጊዜ አጠቃቀም የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

### ናርዶስና ልዑል

ሁለቱም የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ጊዜያቸውን ለትምህርት፣ ለጥናት፣ ለመዝናናትና ቤተሰብን ለማገዝ በማለት ከፋፍለው መድበዋል። ለትምህርት በመደቡት ጊዜያቸው ሰዓታቸውን አክብረው ወደትምህርት ቤት በመሄድ በትምህርት ገበታቸው ላይ ይገኛሉ።

በክፍል ውስጥም እያንዳንዱን የትምህርት አይነት በንቃት ይከታተላሉ። መምህሮቻቸው የሚሰጧቸውን የቤት ስራ በአግባቡ ሰርተው ስለሚመጡ ሁል ጊዜም በትምህርታቸው ቀዳሚ ናቸው። ከትምህርት ቤት ያለበቂ ምክንያት መቅረት አይወዱም። የትምህርት ጊዜን ማክበር ለህይወታቸው ትልቅ ትርጉም እንዳለው ያውቃሉ።

**ከላይ ከቀረበው ከነናርዶስና ከልዑል ታሪክ ምን ተረዳችሁ? ቀጥሎስ ስለ ምን የሚቀርብ ይመስላችኋል?**

ናርዶስና ልዑል ከትምህርት ቤት ሲመለሱ የደንብ ልብሳቸውን ቀይረው ትንሽ እረፍት ካደረጉ በኋላ ማጥናት ይጀምራሉ፡፡ የተሰጣቸውንም የቤት ስራ አብረው ይሰራሉ፡፡ ያልገባቸውንም ነገር ይጠያየቃሉ፡፡ወላጆቻቸው የገዙላቸውን አጋዥ መፅሐፎች ያነባሉ፡፡ በሚያጠኑበት ጊዜ ሁለቱም ያልገባቸው ነገር ካለ መዝግበው በመያዝ መምህሮቻቸውን ይጠይቃሉ፡፡

የጥናት ጊዜያቸውንና የቤት ስራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ከጓደኞቻቸው ጋር ይጫወታሉ፡፡ በትርፍ ጊዜያቸው ወደመዝናኛ ስፍራ ይሄዳሉ፡፡ ባላቸው ትርፍ ጊዜ አቅማቸው የሚፈቅደውን ስራ በማገዝ ከቤተሰብ ጋር ያሳልፋሉ፡፡

**ተግባር አንድ ፦ አንብቦ መረዳት**

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡ መሰረት በማድረግ በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. በክፍል ውስጥ እያንዳንዱን ትምህርት በንቃት መከታተል ለምን ያስፈልጋል?
2. ከትምህርት ቤት ያለ በቂ ምክንያት መቅረት ሊያስከትለው የሚችለው ጉዳት ምንድን ነው?
3. ናርዶስና ልዑል ጊዜያቸውን በአግባቡ ይጠቀማሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?
4. እናንተ ብትሆኑ ስታጠኑ ያልገባችሁን ነገር ማንን ትጠይቃላችሁ?

### ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ መልሱን በፅሑፍ አስፍሩ።

1. ‹‹ናርዶስና ልዑል›› ከሚለው ምንባብ የተረዳችሁትን ፍሬ ሃሳብ በአራት አረፍተ ነገሮች በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡
2. እናንተ ጊዜያችሁን እንዴት እየተጠቀማችሁበት እንደሆነ በአምስት ዓረፍተ ነገሮች ፃፉ፡፡

**ተግባር ሁለት፦ ቃላት**

**ከዚህ በታች በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ቃላት ወይም ሀረጋት በመምረጥ የተጓደሉትን አረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ።**

| | | |
|---|---|---|
| ጥቃቅን | ጢም ብሎ | ስራ |
| ትኩረት | መምህር | ጥቅም |

1. ውሃው__________ሞላ፡፡
2. __________የእውቀት አባት ነው፡፡
3. __________የሰው ልጆች ህልውና ነው፡፡
4. __________ጉዳዮች ከአላማችን ሊያስቀሩን አይገባም፡፡
5. ጊዜን በአግባቡ__________ላይ ማዋል ተገቢ ነው፡፡
6. በህይወታችን__________መስጠት ያለብን ለወሳኝ ጉዳዮች ነው፡፡

## ክፍል አራት፡- ቃላት

**ተግባር አንድ፦ የተውሶ ቃላት**

ቴሌቪዥን፣ ጳጳስ፣ ሬዲዮ፣ ጉዲፈቻ፣ ኢንተርኔት፣ አባወራ፣ ቀበቶ፣ሸሚዝ፣ተ ሞባይል ወዘተ. አማርኛ ቋንቋ ከሌሎች ቋንቋዎችየተዋሳቸው ቃላት ናቸው፡፡

**ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች የቀረቡትን የተውሶ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡**

1. ፖሊስ
2. እንስት
3. ዩኒቨርሲቲ
4. ፖስታ
5. ሰንጋ
6. ፓስታ

## ክፍል አምስት፡- ጽሕፈት

**ተግባር አንድ፡ ፡- መፃፍ**

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ በጽሑፍ አስፍሩ፡ ፡**

1. እያንዳንዳችሁ ከጠዋት እስከ ማታ የምታከናውኗቸውን ተግባራት በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡
2. ‹‹ጊዜ ወርቅ ነው›› የሚለው አባባል ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፍ ሰዎችን ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

**ለ. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተ ነገሮች አዳምጣችሁ በመፃፍ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡**

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

**ተግባር አንድ፡ ግሶችን መለየት**

**ማስታወሻ**

ግስ በዓረፍተ ነገር መጨረሻ በመግባት ዓረፍተ ነገርን የሚያስር ወይም የሚቋጭ የቃል አይነት ነው፡፡
ምሳሌ፡-
ሀ. ታማኝነት የመልካም ዜጋ መገለጫ ነው፡፡
ለ.ተማሪዎች ንፅህናቸውን ይጠብቃሉ፡፡

ሀ. ባለፈው ምዕራፍ ስለስሞች ተምራችኋል። የተማራችሁትን በማስታወስ ከዚህ በታች የተዘሩትን ስሞች እየመረጣችሁ በሰንጠረዡ ውስጥ በአይነት መድቧቸው።

ብርቱካን፣ ጣና፣ መንደሪን፣ ፍየል፣ ፕሪም፣ በግ፣ ጎንደር፣ ሎሚ፣ ሃና፣ ቢሾፍቱ፣ ነስረዲን

| የፍራፍሬ ስሞች | የሃይቅ ስሞች | የእንስሳት ስሞች | የቦታ ስሞች | የሰው ስሞች |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

ለ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች በማስመር ለዩ።

1. አዳም ጎበዝ ሀኪም ነው።
2. የአድዋ ድል ዘላለም ሲዘከር ይኖራል።
3. ከተማችን የተለያዩ ብሄር ብሔረሰቦች መኖሪያ ናት።
4. ኮምፒዩውተር የተለያዩ ስራዎችን ለመስራት ያስችላል።
5. በውይይት ወቅት የሰዎችን ሀሳብ መረዳት ያስፈልጋል።

## ሐ. ከዚህ በታች በሰፈሩት የቃላት ዝርዝር ውስጥ ግስ የሆኑትን ለይታችሁ አስምሩባቸው።

1. መኪና፣ ነበር፣ ይሆናል፣ ልደታ፣ ክፉኛ
2. ባረፈ፣ መንገዝ፣ አቀረበ፣ ሞባይል፣ ደግ
3. ሶስተኛ፣ ገለጠ፣ መካኒሳ፣ ጊዜ፣ ተጠቀመ
4. ስሩ፣ ሚዛን፣ አገዘ፣ አማርኛ፣ ጠረጴዛ
5. ሻይ፣ ናቸው፣ ሳይንስ፣ ጠጣ፣ ጎበዝ

## መ. ከዚህ በታች የሰፈሩትን ግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ።

1. በላ
2. ወረደ
3. ጠለፈ
4. አወዛወዘ
5. ሄደ
6. ገባ

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

1. ጊዜን በአግባቡ መጠቀም የሚሰጠውን ጠቀሜታ ወላጆቻችሁን ጠይቃችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃላችሁ አቅርቡ፡፡
2. እያንዳንዳችሁ የጊዜ አጠቃቀማችሁን በተመለከተ ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡
3. አማርኛ ቋንቋ ውስጥ በውሰት የገቡ አምስት ቃላት ፃፉ፡፡
4. በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች ለይታችሁ አስምሩባቸው፡፡

   ሀ. እህቴ ልብሷን አጠበች፡፡

   ለ. ልጁ በጠዋት ተነስቶ ቁርሱን በላ፡፡

   ሐ. ቅድስት ፀጉሯን አበጠረች፡፡

   መ. ጊቤ ትልቅ ወንዝ ነው፡፡

   ሠ. አለሙ በፍጥነት አነበበ፡፡

አማርኛ

፫ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አምስት
## መጓጓዣ

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የተሰጣችሁን ምንባብ መሰረት ያደረገ ዘገባ ታቀርባላችሁ፡፡
- የተሰጣችሁን ምንባብ በጥልቀት በማንበብ ከተጨባጭ ህይወታችሁ ጋር ታገናኙታላችሁ፡፡
- የተዘበራረቁ ዓረፍተ ነገሮችን አስተካክላችሁ ትፅፋላችሁ፡፡
- የስም ገላጮችን ትለያላችሁ፡፡
- ለቃላት ፍች ትሰጣላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

### <<የመጓጓዣ አይነቶችና አገልግሎታቸው>>






**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ስለመጓጓዣ ምንነትና አገልግሎት የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
3. እናንተ ምን አይነት የመጓጓዣ አይነቶችን ትጠቀማላችሁ?

ተግባር

አንድ፡- አዳምጦ መረዳት

**በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ከአዳመጣችሁት ምንባብ የተረዳችሁትን ሀሳብ በቃል ግለፁ፡፡
2. ለመጓጓዣነት ያገለግላሉ የተባሉት ምን ምን ናቸው?
3. የየብስ መጓጓዣ ሲባል ምን ማለት ነው?
4. የባህላዊ መጓጓዣ ምንነትን ከገለፃችሁ በኋላ በምሳሌ አስረዱ፡፡

ተግባር ሁለት፡- ቃላት

**ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች በጽሑፍ ስጡ፡፡**

1. መርከብ በአንድ ጊዜ ብዙ እቃዎችን ይጭናል፡፡
2. የየብስ መጓጓዣዎች ለማህበረሰቡ ሰፊ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡
3. ዘመናዊ መጓጓዣዎች ከባህላዊ መጓጓዣዎች ይልቅ ፈጣን ናቸው፡፡
4. መጓጓዣዎች ጭነት ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡
5. ከቴክኖሎጂ መስፋፋት ጋር ተያይዘው የመጡ የትራንስፖርት መገልገያዎች በርካታ ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር


**ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መናገር**

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. የባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣ አይነቶችን አንድነትና ልዩነት በቃል ተናገሩ፡፡
2. መጓጓዣዎች የየብስ፣ የአየርና የውሃ ተብለው ይከፈላሉ፡፡ ስለ እያንዳንዳቸዉ ዘርዝራችሁ ተናገሩ፡፡
3. መጓጓዣዎች ቁሳቁስንና ሰውን ከማጓጓዝ በተጨማሪ የሚሰጡትን ጥቅም በቡድን ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ የቡድኑን ሃሳብ በአንድ ተወካይ ተማሪ አማካኝነት ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሶስት ፡- ንባብ

### የመንገድ ላይ ደህንነት



**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. ስዕሉን ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ ግለፁ፡፡
2. አንድ ሰው መንገድ ሲያቋርጥ ማድረግ ያለበትን ጥንቃቄ ተናገሩ፡፡
3. የመንገድ ላይ ደህንነት ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል ?

### የመንገድ ላይ ደህንነት

ከቤታችን ወጥተን ወደየትኛውም ቦታ ስንሄድና ስንመለስ መንገድ ከማቋረጣችን በፊት በመጀመሪያ በመንገዱ ጠርዝ ላይ በመቆም የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ እስኪቆም መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ከመሻገራችን በፊት ግራና ቀኝ አቅጣጫን መመልከት ተገቢ ነው፡፡ ምንም እንኳ አሽከርካሪው ቢያየንም ለመሻገር መቸኮል ለአደጋ ስለሚያጋልጥ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም አሽከርካሪው ፍጥነቱን ለመቀነስና ለመቆም በቂ ጊዜ ስለሚያስፈልገው ነው፡፡ እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ የተሽከርካሪዎች ፍሰት ያለበት አካባቢ እንቅስቃሴ በምናደርግበት ጊዜ አሽከርካሪዎችም ላያዩን ስለሚችሉ ለራሳችን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

ለእግረኞች በተፈቀደ መንገድ ላይ በምንሄድበት ወቅት ለእግረኞች

የወጡ ህጎችንና ደንቦችን ማክበር ይኖርብናል፡፡ አለበለዚያ ለአደጋ ተጋላጭ እንሆናለን፡፡ በዚህም አደጋ ምክንያት ክቡር የሆነውን ሕይወታችንን እስከማጣት እንደርሳለን፤ ለአካል ጉዳትም እንጋለጣለን፤ ንብረታችንም ሊወድም ይችላል፡፡

**አንድ ሰው መንገድ ሲያቋርጥ ምን አይነት ስህተቶችን የሚፈፅም ይመስላችኋል?**

በአጠቃላይ እግረኞች መንገድ ሲያቋርጡ ከሚፈፅሟቸው ስህተቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ተሽከርካሪ መቆሙን ሳያረጋግጡ መሻገር

፣ተሽከርካሪ ተከትሎ መሻገር፣ ለተሽከርካሪ ጀርባ ሰጥቶ መሄድ (ግራችንን ጠብቀን አለመሄድ)፣ በተሽከርካሪ መንገድ ውስጥ ገብቶ መሄድ ወይም መሮጥ፣ ለእግረኞች ባልተፈቀደ መንገድ መሻገር፣ የእግረኛ መንገድ እያለ በእግረኛ መንገድ አለመጠቀም፣ ትኩረትን በመንገዱ ላይ ብቻ አድርጎ አለመጓዝ፣ አሽከርካሪ ይጠነቀቅልኛል ብሎ መዘናጋት፣ የትራፊክ መብራትና ምልክቶችን አለማክበር እና በተሽከርካሪ መንገድ ላይ መጫወት ይገኙበታል፡፡ ስለዚህ እኛም ከላይ የተጠቀሱትን ስህተቶች ባለመፈጸም እራሳችንን ከትራፊክ አደጋ መጠበቅ ይኖርብናል፡፡

የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣንና ትምህርት ሚኒስቴር ካዘጋጁት
ለማስተማሪያነት በሚያመች መልኩ የተዘጋጀ

## ተግባር አንድ ፡- አንብቦ መርዳት

### ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃል መልሱ፡፡

1. የምንባቡን ሃሳብ በዝርዝር ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ሰዎች ለእግረኞች የወጣውን ህግ ባያከብሩ ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

3. በመንገድ ላይ ስትንቀሳቀሱ የትኛውን መስመራችሁን ትይዛላችሁ?

4. መንገድ ስትሻገሩ የምታደርጉትን ጥንቃቄ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት በጽሑፍ መልሱ።**

1. የትራፊክ አደጋ መንስኤው የአሽከርካሪዎች ብቻ ነው።

2. በተሽከርካሪ መንገድ ላይ መጫወት ለአደጋ ያጋልጣል።

3. ህፃናት መንገድ ሲያቋርጡ የአዋቂዎችን እጅ ይዘው መሆን አለበት።

4. አሽከርካሪው ካየን በማንኛውም ሁኔታ መንገድ ብናቋርጥ አደጋ ሊደርስብን አይችልም።

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ፡፡**

1. የሚሄድበት

2. መሻገር

3. ማነጋገር

4. ማስተዋል

5. ስህተት

**ለ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቻቸውን ፃፉ።**

1. የትራፊክ ህጎችን መተላለፍ ለአደጋ ያጋልጣል።

2. ዜብራ ለእግረኛ መሸጋገሪያ ተብሎ የተሰመረ ምልክት ነው።

3. ጠዋትና ማታ የተሽከርካሪዎች ፍሰት ይበዛል፡፡

4. የትራፊክ አደጋ ለህይወት መቀጠፍ መንስኤ ነው፡፡

5. የመንገድ ጠርዝ ላይ በመቆም ተሽከርካሪዎች እስኪያልፉ መጠበቅአስፈላጊ ነው፡፡

**ተግባር ሶስት፡- ጽሕፈት**

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን በጽሑፍ መስርቱ፡፡**

1. መጫወት
2. ትኩረት
3. ሰላም
4. ኮሮና
5. ግብር
6. ታታሪ

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትዕዛዙን መሰረት በማድረግ በጽሑፍ መልሱ፡፡**

1. በአካባቢያችሁ በብዛት ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው የመጓጓዣ አይነት የትኛው ነው? ለምን ?

2. የትራፊክ አደጋ እንዳይደርስባችሁ ለመከላከል የምታደርጉትን ጥንቃቄ በሶስት አረፍተ ነገሮች በመፃፍ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍል አራት፡- ቃላት

### ተግባር አንድ፡- የቃላት ፍች

**ሀ. ቀጥሎ በ <<ሀ>> ስር ለቀረቡት ቃላት ከ <<ለ>> ስር ተመሳሳይ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ።**

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| 1. አከተመ | ሀ. ፋፋ |
| 2. ወፈረ | ለ. ተጣመረ |
| 3. ተቆራኘ | ሐ. አበቃ |
| 4. ጉልህ | መ. ረዥም |
| 5. መለሎ | ሠ. ግዙፍ |

**ለ. ቀጥሎ በ <<ሀ>> ስር ለቀረቡት ቃላት ከ <<ለ>> ስር ተቃራኒ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ።**

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| 1. መነመነ | ሀ. ውድቅት |
| 2. ቀትር | ለ. ቧልት |
| 3. ቁምነገር | ሐ. ወፈረ |
| 4. አስከፋ | መ. ታች |
| 5. ላይ | ሠ. አስደሰተ |
| 6. ቋጠረ | ረ. ፈታ |

ሐ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

1. ሶስና በትምህርቷ አመርቂ ውጤት አስመዘገበች፡፡

2. ያሲን የሶስተኛ ክፍል ተወካይ ሆኖ ተመረጠ፡፡

3. ለፈተና በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

4. ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሃብት የታደለች ሀገር ናት፡፡

5. ጨዋታ ስንጫወት ህጎቹን ማክበር አለብን፡፡


መ. ከዚህ በታች የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ቃላቱን በማጣመር አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ስነምግባር

ለ. ስነቃል

ሐ. ስነዜጋ

መ. ስነጥበብ





ምሳሌ፡-ሀ. ቤተ መንግስት

ለ.

ሐ.

መ.

ሠ.



## ክፍል አምስት፣ ጽሕፈት

### ተግባር አንድ፡- መፃፍ

**ሀ. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት ቅደም ተከተል በማስያዝ አረፍተ ነገሮችን ፃፉ፡፡**

1. አጥቦ ለበሰ ሰመረ ተኩሶ ሸሚዙን፡፡
2. ጓደኛ የሜሮን መጣች ወደ ቤት፡፡
3. ነው ስፖርት ጠቃሚ ለጤና ፡፡
4. ጎበዝ ናት ደራርቱ አትሌት፡፡
5. አልሃምዱ ነው ሰራተኛ ታታሪ፡፡

**ለ. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በድርጊት ቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡**

ምሳሌ፡-

ሀ. ወደሚቀጥለው ክፍል ተዛወረ፡፡

ለ. ጥሩ ውጤት አመጣ፡፡

ሐ. ሂማኦል ጠንክሮ አጠና፡፡

ከላይ ከ‹‹ሀ›› እስከ ‹‹ሐ›› የቀረቡት አረፍተ ነገሮች በቅደም ተከተል ሲፃፉ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ሂማኦል ጠንክሮ አጠና፡፡ ጥሩ ውጤት አመጣ፡፡ ወደሚቀጥለው ክፍል ተዛወረ፡፡

1. ትምህርት ቤት ገባች፡፡
2. በርትታ አጠናች፡፡
3. ኤልዳና ሰባት አመት ሞላት፡፡
4. ከክፍል አንደኛ ወጣች፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- ገላጮችን መለየት

**ማስታወሻ**

ገላጮች ከስም በፊት ወይም በኋላ በመግባት ስምን ይገልፃሉ። ምሳሌ፡- ትልቅ፣ ትንሽ፣ ቀይ፣ ሰማያዊ፣ ሞላላ፣ አረንጓዴ ወዘተ የስም ገላጮች ናቸው።

**ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ገላጮች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ለይታችሁ አስምሩባቸው።**

ምሳሌ፡-

ሀ. እኔ <u>ቀይ</u> ሹራብ አለኝ።

ለ. ሳምሶን <u>ጎበዝ</u> ተማሪ ነው።

1. ረባሹ ልጅ ተቀጣ።
2. መሬት ክብ ናት።
3. ሀይሌ ድንቅ አትሌት ነው።
4. ትንሽ ድመት አየሁ።
5. ሙባረክ ጥሩ ብሬል ገዛ።

**ለ. ከዚህ በታች በቀረቡት ገላጮች አረፍተ ነገሮችን በጽሑፍ መስርቱ።**

1. አረንጓዴ
2. ሰነፍ
3. ትልቅ
4. አሮጌ
5. ወፍራም

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትዕዛዙን መሰረት በማደረግ መልስ ስጡ።**

1. መንገዝ ባይኖር የሰው ልጅ ሊገጥመው የሚችለውን ችግር ወላጆቻችሁን ወይም የምታውቁትን ሰው ጠይቃችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. የመንገድ ላይ ደህንነት ሲባል ምን ማለት ነው? የሳይንስመምህራችሁን ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

3. ከዚህ በታች በቀረቡት ገላጮች አረፍተ ነገር መስርቱባቸው።

ሀ. ቀጭን

ለ. ፈጣን

ሐ.ጣፋጭ

4. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በድርጊት ቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ፃፉ።

ሀ. በሚገባ ደጋግማ አጠበች

ለ. ገነት ቡና ገዛች።

ሐ. በማሽን ፈጬች።

መ. አፍልታ ከእናቷ ጋር ጠጣች።

ሠ. በጥንቃቄ ቆላች።

5. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ፃፉ።
ሀ. ማወዳደር

ለ. ተኮፈሰ ሐ. አስተዋለ

# ምዕራፍ ስድስት
# ሥነ ምግባር

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ከአዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ጠቃሚ ነጥቦችን ትናገራላችሁ።
- ከአነበባችሁት ምንባብ ውስጥ ጥሩና መጥፎ ስነ ምግባሮችን ትለያላችሁ።
- ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ተጠቅማችሁ ዓረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ።
- ለቃላት ፍች ትሰጣላችሁ።

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

### አቶ አየለና አታላዩ ሰውዬ



**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን መልዕክት ለመምህራችሁ በቃል ተናገሩ፡፡
2. ‹‹አቶ አየለና አታላዩ ሰውዬ›› ከሚለው ርዕስ በመነሳት ስለምን የምታዳምጡ ይመስላችኋል?
3. አንድ ሰው ታማኝ ነው የሚባለው ምን ሲያደርግ ይመስላችኋል?

**ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት**

**ሀ. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሃሳብ በቃል ተናገሩ፡፡
2. አቶ አየለ አታላዩን ሰውዬ ያገኘው የት ነው?
3. አታላዩ ሰው ወደ አቶ አየለ ቤት መሄድ የፈለገው ለምንድን ነው?
4. በመንገድ ዳር ተኝተው እርዳታን የሚጠይቁ ሰዎች ሁሉ አታላይ ናቸው ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምን?

## ለ. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በፅሁፍ መልስ ስጡ፡፡

1. አቶ አየለ ባታላዩ ሰው የተታለሉት ለምንድን ነው?
2. እናንተ አቶ አየለን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?
3. አታላዩ ሰውዬ በአቶ አየለ ንግግር ልቡ የተነካው ለምንድን ነው?
4. ታማኝነት ያለውን ጠቀሜታ ቤተሰቦቻችሁን ጠይቃችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡላቸው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### ሮዛና ሳሙኤል



### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ በቃል ተናገሩ፡፡
2. ጥሩ ስነ ምግባር ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## ሮዛና ሳሙኤል

ሮዛና ሳሙኤል የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ አንድ ቀን እያጠኑ እያለ እስካሁን ያነበብነውን አንዳችን ለአንዳችን ተራ በተራ እናስረዳ በማለት ተወያዩ፡፡ ከዚያም ሮዛ በመልካም ስነ ምግባር ላይ እንድታቀርብ ሣሙኤል ደግሞ መጥፎ ስነምግባር ላይ እንዲያቀርብ ተስማሙ፡፡ ሃሳባቸውንም እንደሚከተለው በመጠያየቅ ጀመሩ፡፡ መልካም ስነ ምግባርን አስመልክቶ የመጀመሪያ ጠያቂ ሳሙኤል ነበር፡፡

ሳሙኤል፡- ‹‹መልካም ስነ ምግባር ማለት ምን ማለት ነው?››

ሮዛ፡- ‹‹መልካም ስነ ምግባር ማለት መልካም ፀባይ ወይም ባህሪ ያለው ሰው ነው፡፡ ህብረተሰባችን የሚወደውና የሚቀበለው ማንኛውም ዓይነት መልካም ተግባር ነው፡፡››

ሳሙኤል፡- ‹‹ለመሆኑ አንድ ሰው መልካም ስነ ምግባር እንዳለው በምን ይታወቃል?››

ሮዛ፡- ‹‹መልካም ስነ ምግባር ያለው ሰው ትላልቅ ሰዎችን ያከብራልአቅመ ደካሞችን ይረዳል፤ ስራውን በአግባቡ ይሰራል፤ አካባቢውን ይንከባከባል፤ አይዋሽም፤ አያታልልም፤ አያጭበረብርም፤ ከሰዎችጋር አይጣላም፤ ጊዜውን በአግባቡ ይጠቀማል፡፡ መልካም ስነ ምግባር ያለው ሰው ሀገሩን ይወዳል፤ የተቸገረን ይረዳል፡፡››

### ስለ መጥፎ ስነ ምግባር ምን ምን ጉዳዮችን የሚያነሱ ይመስላችኋል?

ሮዛ፡- ‹‹ጥያቄህን ጨርሰህ ከሆነ እኔ ልቀጥል፡፡››

**ሳሙኤል**፡- ‹‹አዎ አሁን አንቺ ጠይቂኝ፡፡››

ሮዛ፡- ‹‹መጥፎ ስነ ምግባር ምንድን ነው?››

ሳሙኤል፡- ‹‹መጥፎ ስነ ምግባር መጥፎ ተግባር ሲሆን ህብረተሰባችን
የማይወደውና የማይቀበለው ነው፡፡››

ሮዛ፡-‹‹መጥፎ ስነ ምግባር ያለው ሰው እንዴት ይታወቃል?››
ሳሙኤል፡- ‹‹መጥፎ ስነ ምግባር ያለው ሰው ከሰዎች ጋር
አይስማማም በሆነው ባልሆነው ይጣላል፡፡ ወላጆቹንም
ሆነ ሌሎችሰዎችን አያከብርም፤ ደካሞችን ይንቃል፤
ጊዜውንበአግባቡ አይጠቀምም፤ አታላይና አጭበርባሪ
ነው፤ይዋሻል፤ ሀላፊነቱን በአግባቡ አይወጣም፡፡ እንደዚህ
አይነት ባህሪ ያላቸውን ሰዎች ሰው አይወዳቸውም፡፡››

ሮዛ፡- ‹‹መልካም ስነ ምግባርን ማን ሊያስተምር ይችላል?››

ሳሙኤል፡- ‹‹ወላጆችና ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ ወላጆች
ልጆቻቸውን መልካም ስነ ምግባር እንዲኖራቸው በስነ ስርዓት
ኮትኩተው ማሳደግ ይኖርባቸዋል፡፡ ትምህርት ቤቶችም ጥሩ
ትውልድ ለማፍራት መልካም ስነ ምግባርንበማስተማር
ትልቅ አስተዋፅኦ ማድረግ አለባቸው፡፡››

ሮዛ፡- ‹‹ጥያቄዎቼን ጨርሻለሁ አንተ የምትጨምረው አለ?››
ሳሙኤል፡- ‹‹እኔም ጨርሻለሁ ፡፡ ለዛሬ እስካሁን የተወያየነው
ይበቃናል አሁን ትንሽ ማረፍ ይኖርብናል››

ሮዛ ፡- ‹‹እውነት ብለሃል እኔም ስለደከመኝ ማረፍ እፈልጋለሁ፡፡
መልካም የእረፍት ጊዜ ጓደኛዬ፡፡››

ሳሙኤል፡- ‹‹ላንቺም መልካም እረፍት››

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃል መልሱ።**

1. ምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱት ባለታሪኮች እነማን ናቸው?
2. መልካም ስነ ምግባር ማለት ምን ማለት ነው?
3. አንድ ተማሪ ጥሩ ስነ ምግባር እንዲኖረው ምን ማድረግ አለበት?
4. አንድ ሰው መጥፎ ስነ ምግባር አለው የሚያስብሉት ባህሪያት ምን ምን ናቸው?

## ተግባር ሁለት፡- ቃላት

**ሀ. ቀጥሎ በ <<ሀ>> ስር ለቀረቡት ቃላት ከ <<ለ>> ስር ተመሳሳይ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ተወያዩ | ሀ. ሚና |
| 2. ፀባይ | ለ. ተመካከሩ |
| 3. ይረዳል | ሐ. ባህሪ |
| 4. አስተዋፅኦ | መ. አበቃ |
| 5. ጨረሰ | ሠ. ያግዛል |

**ለ. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ቀጥሎ በተሰጡት ቃላት አሟልታችሁ ፃፉ።**

| | | |
|---|---|---|
| ስነ ምግባር | ትውልድ | ማገዝ |
| አይዋሽም | ኀላፊነት | ይንከባከባል |

1. የእኛ______________የራሱን አሻራ ማሳረፍ አለበት።
2. መልካም ዜጋ___________ይሰማዋል።
3. ልጆች ከህፃንነታቸው ጀምሮ መልካም______መማር አለባቸው።
4. መልካም ስነ ምግባር ያለው ሰው የተፈጥሮ ሃብቶችን_______።
5. በዙሪያችን ያሉ አቅመ ደካሞችን______የሁላችንም ግዴታ ነው።

**ተግባር ሁለት፡- መፃፍ**

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሑፍ መልሱ፡፡**

1. ከምንባቡ የተረዳችሁትን ሀሳብ በሶስት አረፍተ ነገሮች ግለፁ፡፡
2. መልካም ስነ ምግባር የሚጠቅመው ማንን ነው? ለምን?
3. መጥፎ ስነ ምግባር የሚጎዳው ማንን ነው? ለምን?

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

**ተግባር አንድ፡- የቃላት ፍች**

**ሀ. ቀጥሎ በ <<ሀ>> ስር ለቀረቡት ቃላት ከ <<ለ>> ስር ተቃራኒ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አሞካሸ | ሀ. ፅድቅ |
| 2. ተነታረከ | ለ. አበላሸ |
| 3. አሳመረ | ሐ. ገለጠ |
| 4. ጋረደ | መ. ተስማማ |
| 5. ኩነኔ | ሠ. አጥላላ |

**ለ. ለሚከተሉት ቃላት ከሳጥኑ ውስጥ ተስማሚ የሆኑ ተጣማሪ ቃላትን በመምረጥ አጣምሩ፡፡**

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሳጥን | አበር | ደንብ | ሰፊ | ተከተል | ቀር | ቀደም |

ምሳሌ፡- ኋላ ቀር

1. ኋላ
2. ቁም
3. ግንባር

4. ቅደም
5. ግብረ
6. ህገ
7. ልብስ

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ተግባር አንድ፡- መፃፍ

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በመጠቀም አሟልታችሁ ፃፉ።**

| አራት ነጥብ (።) | ጥያቄ ምልክት (?) | ቃለ አጋኖ (!) | ትዕምርተ ጥቅስ (‹‹ ››) | ሁለት ነጥብ (፡) | ነጠላ ሰረዝ (፣) |
|---|---|---|---|---|---|

1. የፈተናው ቀን መቼ ነው
2. ሰውን ሰው ያደረገው ስራ ነው አለች አያቴ
3. ግብርና የሀገራችን ኢኮኖሚ ዋልታ ነው
4. ጎሽ ስራ ፈጣሪ በመሆኑ ተሸለመ
5. ጠዋት ትምህርት የሚጀመረው 2 30 ነው

**ለ. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ስርአተ ነጥቦች በመጠቀም በቀረቡት ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱ።**

| ‹‹ ›› | ። | ፣ | ! | ? | ፡ |
|---|---|---|---|---|---|

1. መፍትሔ
2. አባይ
3. ቆጠበ
4. ትዕግስት
5. ይቅርታ

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- ተውሳከ ግስ

**ማስታወሻ**

ተውሳከ ግስ በሌላ ስሙ የግስ ገላጭ ተብሎ የሚጠራ ነው፡፡

ተውሳከ ግስ ከግስ በፊት በመግባት ስለግሱ ተጨማሪ መረጃ የሚሰጥ ቃል ነው፡፡

ምሳሌ፡- ክፉኛ፣ ቶሎ፣ ምንኛ፣ ገና፣ መቼ፣ እንዴት የመሳሰሉት ተውሳከ ግስ ናቸው፡፡

በአረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

ሀ. አቤሴሎም ቶሎ መጣ፡፡

ለ. ልጁ እግሩን ክፉኛ ታሟል፡፡

**ከዚህ በታች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ተውሳከ ግስ ቃላትን በማስመር ለዩ፡፡**

1. መምህራችን መቼ መጡ?
2. ታክሲው ገና አልደረሰም፡፡
3. ቃለአብ ከእንቅልፉ ቶሎ ነቃ፡፡
4. የወላጆች በዓል ነገ ይከበራል፡፡
5. ዳንኤል እንዴት መጣህ?

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትዕዛዙን መሰረት በማድረግ መልስ ስጡ፡፡**

1. ስለመልካምና መጥፎ ስነ ምግባር በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የሚተላለፉ መልዕክቶችን አዳምጣችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተርኩላቸው፡፡
2. ስለመልካም ስነምግባር የሚተርኩ ተረቶችን ፈልጋችሁ በማንበብ ፍሬ ሀሳቡን ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አንብቡላቸው፡፡
3. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ፡፡

    ሀ. ውድ

    ለ. ቅርብ

    ሐ. ማስረዘም
4. የሚከተሉትን ስርዓተ ነጥቦች በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

    ሀ. አራት ነጥብ (፡፡)

    ለ. ጥያቄ ምልክት (?)

    ሐ. ትዕምርተ ጥቅስ (‹‹ ››)
5. ከዚህ በታች በቀረቡት የቃላት ዝርዝር ውስጥ ተውሳከ ግስ የሆኑ ቃላትን ለይታችሁ ፃፉ፡፡

    ሀ. አበበ፣ ገና፣ ሄደ፣ ምንኛ፣ ቢጫ፣ ትምህርት ቤት

    ለ. ክፉኛ፣ ሬዲዮ፣ ቶሎ፣ መቀሌ፣ መቼ

አማርኛ

፫ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሰባት
# ግብርና

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የአዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚና ጨዋታ ትጫወታላችሁ፡፡
- ከአነበባችሁት አንቀፅ ውስጥ ዋናውን ሀሳብ ትፅፋላችሁ፡፡
- የአነበባችሁት ምንባብ ውስጥ ያገኛችሁትን ዋና ጉዳይ ትፅፋላችሁ፡፡
- ለአዳዲስ ቃላት ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡
- ከጽሑፍ ውስጥ ተውሳከ ግሶችን ትለያላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

## የከተማ ግብርና



**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ስዕሉን ስትመለከቱ ስለምን የምታዳምጡ ይመስላችኋል?
2. የ‹‹ከተማ ግብርና›› ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
3. የጓሮ አትክልት ሲባል ምን ማለት ነው?

**ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት**

**ሀ. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳችሁን በቃል ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡**

1. በከተማ ግብርና ውስጥ ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራት ምን ምን ናቸው?
2. የምንባቡን አጠቃላይ ሃሳብ አሳጥራችሁ በቃላችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
3. በግብርና ላይ ለመሰማራት የባለሙያ ምክር ለምን ያስፈልጋል?
4. አንድ የከተማ ኗሪ ከግብርና ዘርፍ የሚያገኘው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

## ለ. ከዚህ በታች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለጥያቄዎቹ በፅሁፍ መልስ ስጡ፡፡

1. እናንተ በምትኖሩበት ግቢ ውስጥ የጓሮ አትክልቶችን ትተክላላችሁ? መልሳችሁን በምክንያት በማስደገፍ ፅፋችሁ አቅርቡ፡፡
2. በግብርና በመሰማራት እንዴት የምግብ ፍጆታችንንና ገቢያችንን ማሳደግ እንችላለን? ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡
3. ለምግብነት የምትጠቀሙባቸውን አትክልቶች የምታገኙት ከየት ነው? ወላጆቻችሁን ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

## ሀ. ለሚከተሉት አዳዲስ ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከሰንጠረዡ እየመረጣችሁ አዛምዱ፡፡

| | |
|---|---|
| ሰብል | ድርሻ |
| ማሳ | ዘዴ |
| ማረስረስ | ምርታማ |
| ማጠራቀም | የውሃ ማስተላለፊያ |

1. ውጤታማ ________________
2. ማርጠብ ________________
3. የእርሻ ቦታ ________________
4. መሰብሰብ ________________
5. ብልሃት ________________
6. ፈንታ ________________
7. ቦይ ________________
8. አዝመራ ________________

## ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን መስርቱ።

ምርጥ ዘር

ፍጆታ

እሸት

መስኖ

ዘመናዊ

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር አንድ፡- መናገር

**ከዚህ በታች የቀረበላችሁን ጭውውት መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚና ጨዋታውን ተግብሩ።**

ለምሳሌ፡-

ምህረት፡-ኪሩቤል እኔ በትርፍ ጊዜዬ የጓሮ አትክልቶችን አለማለሁ፡፡ አንተስ?


ኪሩቤል፡-አምስት እንቁላል ጣይ ዶሮዎች አሉኝ፡፡ እነሱን እንከባከባለሁ፡፡ ለመሆኑ አንቺ ምን ምን የጓሮ አትክልቶችን ታለሚያለሽ?

ምህረት፡-በአብዛኛው በትንሽ ቦታ ላይ የሚለሙ አትክልቶች ናቸው፡፡ እንደ ቆስጣ፣ ሰላጣ ቲማቲምና ቃሪያ አለማለሁ በእረፍት ጊዜዬ አትክልቶችን በመንከባከብ በማሳለፌ ደስተኛ ነኝ፡፡

ኪሩቤል፡- እኔም በእረፍት ጊዜዬ ከዶሮዎቼ ጋር ነው የማሳልፈው ምግብ አዘጋጅላቸዋለሁ፡፡ ለተለያየ በሽታ እንዳይጋለጡ ቤታቸውን አፀዳለሁ፡፡ እንቁላል መጣያ ቦታቸውንም አመቻቻለሁ፡፡

## ክፍል ሶስት፦ ንባብ

### አይበገሬዎቹ እህትማማቾች



**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. በአካባቢያችሁ ሰዎች በአብዛኛው የሚሰማሩባቸው የስራ አይነቶች ምንድን ናቸው?
3. ‹‹አይበገሬዎቹ እህትማማቾች›› የሚለው ምንባብ ስለምን የሚተርክ ይመስላችኋል?

**አይበገሬዎቹ እህትማማቾች**

በአዲስ አበባ ከተማ አቅራቢያ የሚኖሩ ሶስት እህትማማቾች ነበሩ፡፡

ጎበዝና ታታሪ ወጣቶች ቢሆኑም ስራ ግን አልነበራቸውም፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ‹‹መፍትሄ መፈለግ አለብን ያለ ስራ እስከመቼ እንደዚህ እንኖራለን›› በማለት ተመካከሩ፡፡ ‹‹መማራችን አንዱም የሚጠቅመን ለችግሮቻችን አስበን መፍትሄ ለመፈለግ ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ብልሃት መፈለግ አለብን›› ተባባሉ፡፡ ከዚያም ‹‹‹የእናትና አባታችን መሬት አለ ለምን? እዚያ ላይ አንሰራም መሬቱም ጦም ማደር የለበትም›› በማለት ተስማሙ፡፡ የእናትና አባታቸውን መሬት

በማረስ ለመጠቀም ወሰኑ፡፡ ይሁን እንጂ ለእርሻ ስራው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች አልነበሯቸውም፡፡ ‹‹ለእርሻ ስራው የሚያስፈልጉንን ቁሳቁሶች እንዴትም ብለን ፈልገን ስራውን መጀመር አለብን›› ሲሉ ተወያዩ፡፡ ከዚያም አንድ ቀን በአካባቢው ወደ ሚኖረው አጎታቸው ጋር ሄደው የሚያስፈልጋቸውን የእርሻ መሳሪያ እንዲሰጣቸው ጠየቁ፡፡ አጎታቸውም በሃሳባቸው ተስማምቶ የሚያስፈልጋቸውን የእርሻ መሳሪያዎች አሟላላቸው፡፡ እህትማማቾቹም በተሰጣቸው የእርሻ መሳሪያ በመታገዝ ማሳውን አርሰው ጨረሱ፡፡

መሬቱን አርሰው ከጨረሱ በኋላ እህሉን ለመዝራት መሬቱን

በውሃ ማረስረስ ነበረባቸው፡፡ ቀኑን ሙሉ በጀሪካን እየቀዱ ማሳው ላይ ቢረጩትም የሚፈልጉትን ያህል አልራሰም፡፡ ‹‹እስቲ አንድ መፍትሄ አስቡ›› አለች ትንሿ እህታቸው፡፡ ‹‹ወንዙ ቅርብ ቢሆንም እንደዚህ እየቀዳን ማጠጣት በጣም አስቸጋሪ ነው አለች›› ከዚያም አንድ መፍትሄ ላይ ደረሱ፡፡

**እህትማማቾቹ ምን አይነት መፍትሄን የሚያመጡ ይመስላችኋል?**

የውሃ ማስተላለፊያ የፕላስቲክ ቱቦ ገዝተው በመጠቀም ከወንዙ ወደማሳው ውሃ ማፍሰስ ጀመሩ፡፡ በማሳቸው ላይ የተለያዩ የአዝርዕት አይነቶችን በመዝራት እንክብካቤ ያደርጉላቸው ጀመር፡፡ ማሳው ላይ ከዘሩት የእህል አይነቶችም አንዱ በቆሎ ሲሆን የአፈሩ ለምነትና የሚያደርጉለት እንክብካቤ ስለተመቸው ፍሬያማ ሆነ፡፡

አባታቸው ግን ሴት ልጅ የእርሻ ስራ ላይ ስትሰማራ የተለመደ ባለመሆኑ ተግባራቸውን ይቃወማቸው ነበር፡፡ ሌሎች የመንደሩ ሰዎች ደግሞ ልክ እንደ አባታቸው ሁሉ የሴት ያልሆነን ስራ የሚሰሩ ባለጌዎች እያሉ ይነቅፏቸውና ይጠሏቸው ነበር፡፡

ሶስቱም እህትማማቾች የመጀመሪያውን እሸት ቆርጠው ለእናትና አባታቸው አቀረቡ፡፡ አባታቸው እስከዛሬ በሴትነታቸው ስላንኳሰሳቸው

በጣም አፈረ፡፡ ‹‹ልጆቼ በጣም ተሳስቼ በድያችኋለሁና ይቅርታ አድርጉልኝ›› ብሎ ጠየቃቸው፡፡ እህትማማቾቹ ግን የአባታቸውን ጉልበት እየሳሙ ‹‹አባባ ምንም ብትለን ስላስተማርከን ብቻ ባለውለታችን ነህ፡፡ በመማራችን ደግሞ መላ ፈላጊና ታታሪ ሆንን›› አሉት፡፡ የመንደሩ ሰዎችም ተሰብስበው መጥተው ይቅርታ ጠየቋቸው፡፡ እህሉ ሲደርስም በመሰብሰብ አገዟቸው፡፡ የተሰበሰበውንም እህል ገበያ ወስወደው በመሸጥ ብራቸውን ባንክ ሄደው የቁጠባ ሂሳብ በመክፈት ግማሹን ባንክ አስገቡ፡፡ የቀረውን ለሚፈልጉት ተግባራት አዋሉት፡፡

ምንጭ፡- ዳንኤል ወርቁ (2011 ዓ.ም) የተማሩት እህትማማቾች፣ ተሻሽሎ የተወሰደ

**ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት**

### ሀ. ለሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች መልሳችሁን በቃል ተናገሩ፡፡

1. ከምንባቡ የተረዳችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. በምንባቡ ውስጥ ጦም ማደር የለበትም የተባለው ምንድን ነው?
3. እህትማማቾቹ ለእርሻ ስራ የሚያስፈልጋቸውን ቁሳቁስ ያገኙት ከየት ነው?
4. አንድ ሰው ችግር ሲያጋጥመው ምን ማድረግ ነው ያለበት?

### ለ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን ‘’እውነት’’ ስህተት የሆነውን ደግሞ ‘’ሀሰት’’ በማለት በጽሑፍ መልሱ፡፡ ምክንያታችሁንም በፅሁፍ አስፍሩ፡፡

1. መማር የችግር መፍቻ ቁልፍ ነገር ነው፡፡
2. ስራ መፍጠር የእያንዳንዱ ሰው ሀላፊነት ነው፡፡
3. እህትማማቾቹ ውሃውን በጀሪካን እየተሸከሙ ማረስረስ አልቻሉም፡፡

4. እህትማማቾቹ በመጀመሪያ እሸቱን ያቀመሱት ለጎረቤቶቻቸው ነው፡፡

5. ሶስቱ ሴቶች በሚኖሩበት አካበባቢ ሴት ልጅ ስታርስ የተለመደ አልነበረም፡፡

### ሐ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በጽሑፍ መልስ ስጡ፡፡

1. ከላይ የቀረበውን ምንባብ እንደገና አንብቡና የመጀመሪያውን አንቀፅ ዋና ሀሳብ በራሳችሁ አገላለፅ አሳጥራችሁ ፃፉ፡፡

2. ሴቶች የሚሳተፉባቸው የግብርና ስራዎች ምን ምን እንደሆኑ ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

**ተግባር ሁለት፡- አቀላጥፎ ማንበብ**

### ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ትዕዛዝ መሰረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ፡፡

**ደንና ህይወት**

በድሮ ጊዜ አዕዋፋትና እንስሳት በጋራ የሚኖሩበት ሰፊ ደን ነበር፡ ይህ ደን በልምላሜው የሚታወቅና ለምግብ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ፍራፍሬዎች የሞሉበት ስለነበር የተለያዩ እንስሳትና አዕዋፍ መኖሪያ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ በአካባቢው የሰው ልጆች ከሰፈሩበት ጊዜ አንስቶ ዛፎች ክፉኛ እየተጨፈጨፉና እየተመነጠሩ አለቁ፡፡ በአካባቢውም ዝናብ ጠፋ፡፡ በአቅራቢያው የነበሩት ወንዞችና ምንጮችም እያደር እየቀነሱና እየደረቁ ሄዱ፡፡ መሬትም ተራቆተች፡፡ በዚህ ምክንያት ደኑ ቀስ በቀስ እየተመናመነ ሄደ፡፡ በውስጡ የነበሩት እንስሳትም ምግብ የሚሆናቸውን ፍራፍሬና ስራስሮች ለማግኘት እየተሳናቸው መጡ፡፡ ብዙም ሳይቆይ በአካባቢው ረሀብና ቸነፈር ተከሰተ፡፡

በዚያ ይኖሩ የነበሩት አዕዋፍና እንስሳት በሁኔታው ተደናገጡ፡፡ ከነበሩት ጥቂት ዛፎች የተረፉትን ፍራፍሬዎች በጋራና በቁጠባ

በመቅመስ ትንሽ ወራትን አብረው አሳለፉ። ችግሩ እየበረታ ሲመጣ ጦም ውለው ማደር ጀመሩ። በዚህ የተነሳ በደኑ ውስጥ ይኖሩ የነበሩት እንስሳትና አዕዋፍ ችግራቸውን ለመፍታት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ተወያዩ።

ምንጭ፡- ውዳላት ገዳሙ (ብድሯን ያልከፈለች ወፍ) ተሻሽሎ የተወሰደ

**ተግባር ሶስት፡- ቃላት**

**ከዚህ በታች በቀረበት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ፃፉ።**

1. <u>ጠንክሮ</u> በመስራት መበልጸግ ይቻላል።
2. እንስሳትና አዕዋፍ ደኖች ሲጠፉ መኖር <u>ተሳናቸው</u>።
3. በደኖች መመንጠር ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ድርቅ <u>ተከሰተ</u>።
4. ሰፊው ደን ሙሉ በሙሉ በመውደሙ ከፍተኛ <u>ቸነፈር</u> ተከሰተ።
5. አጎታቸው ለእህትማማቾች የእርሻ መሳሪያ በመስጠት <u>አገዛቸው</u>።
6. በአካባቢያችን <u>የወዳደቁ</u> ቁሳቁሶችን በመጠቀም የውሃ መሳቢያ መስራት ይቻላል።

**ተግባር አራት፡- መፃፍ**

**በአካባቢያችሁ በብዛት የሚመረቱ የአትክልት አይነቶችን ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አንብቡላቸው።**

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### ተግባር አንድ፡- የቃላት ፍች

**ሀ. በ <<ሀ>> ረድፍ ላሉት ቃላት ከ <<ለ>> ረድፍ ተመሳሳይ ፍቺ በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| 1. የሚመነጭ | ሀ. እጅ ሰጠ |
| 2. ተማረከ | ለ. ጫካ |
| 3. ቋጨ | ሐ. የሚነሳ |
| 4. ያላሰለሰ | መ. ዋና ከተማ |
| 5. ደን | ሠ. ጨረሰ |
| 6. መዲና | ረ. ሰጠ |
| 7. ለገሰ | ሰ. የማያቋርጥ |

**ለ. በ <<ሀ>> ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ከ <<ለ>> ረድፍ ተቃራኒ ፍቺ በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ. |
|---|---|
| 1. ብስል | ሀ. ሽቅብ |
| 2. ቁልቁል | ለ. መዳከም |
| 3. መበርታት | ሐ. ጥሬ |
| 4. ወራጅ | መ. ተደፈነ |
| 5. ተሸነቆረ | ሠ. ወጭ |

**ሐ. በሚከተሉት ቃላት ላይ የተጨመሩትን ቅጥያዎች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ለይታችሁ አስምሩ፡፡**

ምሳሌ፡- <u>እየ</u>ሄደ፤ <u>አስ</u>ተማሪ

1. እየፃፈ
2. በሬዎች
3. ሄደች
4. ሲበላ
5. ከመጣ

**መ. በሚከተሉት ቃላት ላይ የተጨመሩትን ቅጥያዎች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ለይታችሁ አውጡ፡፡**

ምሳሌ፡- ፈለገች (-ኧች)

ወንዶች (-ኦች)

1. ወረቀቶች
2. ተማሪዎች
3. ሰራች
4. ቤቶች
5. ተመገበች

## ክፍል አራት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- ተውሳከ ግስ

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ስም፣ የስም ገላጭ፣ የግስ ገላጭና ግስ በማለት ለይታችሁ ፃፉ፡፡**

| ተ.ቁ | አረፍተ ነገር | የስም ገላጭ | ስም | የግስ ገላጭ | ግስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ችኩል ሰው ተረጋግቶ አይሰራም፡፡ | ችኩል | ሰው | ተረጋግቶ | አይሰራም |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ታታሪው ነጋዴ ከአዳማመጣ:: | | | | |
| 3 | አዲሱ ልብስ በጣም ያምራል:: | | | | |
| 4 | ጀግናው ወታደር በድልተመለሰ:: | | | | |
| 5 | ረጅሙ ሰው እየሮጠሄደ:: | | | | |
| 6 | ስስ ወረቀት ቶሎ ይቀደዳል:: | | | | |

## ለ. በ <<ሀ>> ምድብ የቀረቡትን ቃላት በ <<ለ>> ምድብ የቃል ክፍላቸው ጋር አዛምዱ።

ሀ

1. ሀዋሳ
2. ቀጭን
3. ወደቀ
4. ቶሎ

ለ

ሀ. የስም ገላጭ
ለ. ተውሳከ ግስ
ሐ. ግስ
መ. ስም

## ሐ. ከዚህ በታች የቀረቡትን የግስ ገላጮች በመጠቀም አረፍተ ነገሮች መስርቱ።

1. ከፍት
2. በፍጥነት
3. እየሮጠ
4. ምንኛ
5. እንዴት

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. አንድ ስለገበሬና ነጋዴ የሚያወራ ተረት ፈልጋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

2. ‹‹አይበገሬዎቹ እህትማማቾች›› የሚለውን ምንባብ በግላችሁ አንድ ጊዜ ደግማችሁ በማንበብ በእያንዳንዱ አንቀፅ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ሀሳቦች በአራት አረፍተ ነገሮች አሳጥራችሁ ፃፉ።

3. ‹‹ደንና ህይወት›› የሚለው ንምንባብ ውስጥ ፍሬ ሀሳቡን በአንድ አረፍተ ነገር አሳጥራችሁ ፃፉ።

4. ቀጥሎ በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን የግስ ገላጮች ለይታችሁ ፃፉ።

   ሀ. ያስሚን ወደባህር ዳር ሄደች።

   ለ. አብርሃም ስለታመመ አልመጣም።

   ሐ. የአማርኛ ፈተና ነገ ይሰጣል።

5. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

   ሀ. ሀሴት

   ለ. ለኮሰ

   ሐ. አለኝታ

አማርኛ
፫ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ስምንት
# ሥራ

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የአዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ የተነሱ ፍሬ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ንግግር ታደርጋላችሁ።
- ምንባብ አንባባችሁ መልዕክቱን ትረዳላችሁ።
- የወደፊት እቅዳችሁን ትፅፋላችሁ።
- ለአዳዲስ ቃላት ፍች ትሰጣላችሁ።
- ተያያዥነት ያላቸውን አረፍተ ነገሮች ትመሰርታላችሁ።

## ክፍል አንድ፦ ማዳመጥና መናገር

### ታታሪው ሰራተኛ



**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ጥንድ ጥንድ በመሆን ስዕሉን ተመልከቱና የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ታታሪነት በምን የሚገለፅ ይመስላችኋል? ሰዎች ታታሪ ናቸው ሲባሉ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
3. ‹‹ታታሪው ሰራተኛ›› በሚለው ርዕስ ስለምን የምታደምጡ ይመስላችኋል?

## ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት

### ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. መንሱር የተወለደው የት አካባቢ ነው?
2. ባለታሪኩ ከወንድሞቹ የተለየ ያስባለው ምንድን ነው?
3. ለመንሱርና ወንድሞቹ ትምህርት ማቋረጥ ምክንያት የሆነው ምንድን ነው?
4. ታታሪው ሰራተኛ ከሚለው ምንባብ የተረዳችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
5. መንሱር በልጅነቱ ምን መሆን ነበር የሚፈልገው? ፍላጎቱስ ተሳክቶለታል ብላችሁ ታስባላችሁ? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

### ለ. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አረፍተ ነገሮች በሳጥኑ ውስጥ ከተቀመጡት ቃላት ክፍት ቦታዎችን አሟልታችሁ ፃፉ።

ታላላቆቻቸውን፣ ባህል፣ ሀላፊነት፣ ውይይት፣
ነገ፣ ስፖርት፣ ቀልጣፋ

1. ታታሪነት የሁላችንም__________ሊሆን ይገባል፡፡
2. ልጆች__________ማክበር አለባቸው፡፡
3. ብልህ ሰው ስለ__________ያስባል፡፡
4. መፅሀፍትን በአግባቡ መያዝ የሁላችንም__________ነው፡፡
5. ሊዲያ ሁልጊዜም ጠዋት ጠዋት__________ ትሰራለች፡፡
6. በጓደኛሞች መካከል የሚደረግ__________ለውጤት ያበቃል፡፡

## ክፍል ሁለት፣- ንባብ

### ሰነፍ ይከስራል ሰራተኛ ይከብራል



### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ‹‹ሰነፍ ይከስራል ሰራተኛ ይከብራል›› የሚለውን ምንባብ ርዕስ ስታነቡ ምን አስታወሳችሁ? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ.
3. በአካባቢያችሁ በስንፍና ምክንያት ለኪሳራ የተዳረገ ሰው ታውቃላችሁ? ለምን የከሰረ ይመስላችኋል? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡›

### ሰነፍ ይከስራል ሰራተኛ ይከብራል

በድሮ ጊዜ አንድ ሰውዬ ሰው በአለም ላይ ሲኖር ምን ዓይነት ስራ እየሰራ ቢኖር ይሻላል እያለ ሃሳቡን በልቡ ሲያወጣና ሲያወርድ ነበር፡፡ ከዚያም እንዲህ አለ ‹‹መሬት አለኝ፤ ይህንን መሬቴን እህል ብዘራበትና አትክልት ብተክልበት ገንዘብ አገኝበታለሁ፤ መሬቱም ይለማል፡፡ ስለዚህ በሁለት በኩል ጥቅም አገኝበታለሁ›› አለ፡፡

ለዚህም የሚሆነውን ልዩ ልዩ የስራ መሳሪያዎች አሰናድቶ አገልጋዮቹን ጠርቶ ‹‹በመሬቴ ላይ እህል ለመዝራትና የተለያዩ የአትክልት አይነቶችን ለመትከል አስቢያለሁና ስለዚህ ጠዋት ጠዋት ወደዚያ በመሄድ እንድትሰሩ›› ብሎ አዘዛቸው፡፡ ነገር ግን እሱ የትም እየዞረ ሲጠጣ፣ ሲጫወት፣ ሲፈነጥዝ ይውላል፡፡ ሰራተኞችም እሱ እንደሄደ ስለሚያወቁ ጊዜያቸውን በጨዋታ ያሳልፉ ነበር፡፡ ለሶስት ዓመት በዚህ መልኩ ከኖረ በኋላ ከአትክልቱና ከእርሻው ያገኘው ገንዘብ እንኳንስ ሃብት ሊኖረው የአገልጋዮቹን ልብስና ምግብ ሳይችልለት ቀረ፡፡

## የመሬቱ ባለቤት ሰውዬ በቀጣይ ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል?

የመሬቱ ባለቤት ይህ እንዳላዋጣው ሲረዳ የመሬቱን እኩሌታ ሸጠው፤ ሌላኛውን እኩሌታ ደግሞ አከራየው፡፡ የተከራየውም ሰውየ ሶስት ዓመት ሙሉ ለእርሻ፣ ለአትክልትና ለከብት እርባታ እየተጠቀመበት ኪራዩን ይከፍለው ነበር፡፡ ተከራዩም አንድ ቀን ያንን የቀረውን እኩሌታ እንዲሸጥለት ጠየቀው፡፡ ሰውየውም በሃሳቡ ተስማማ፡፡ ‹‹እኔ በዚህ መሬት ሶስት ዓመት ሰርቼ አላተረፍኩበትም፡፡ አንተ ግን ከእኔ ተከራይተህ በየዓመቱ ኪራዩን እየከፈልክ ትርፋማም ሆነህበታል፡፡ ይህም ትርፋማ በመሆንህ ነው የቀረውን ልትገዛ የመጣኸው፡፡ ለመሆኑ ከዚሁ መሬት ነው ወይስ ከሌላ ተበድረህ ባገኘኸው ገንዘብ ነው›› ብሎ ሲጠይቀው ‹‹ባንተ መሬት ላይ ሰርቼ ባተረፍኩት ነው›› ብሎ መለሰለት፡፡ ‹‹እኔ ስከስር አንተ ያተረፍከው እንዴት ነው ምክንያቱን ልትገልፅልኝ ትችላለህ?›› አለው፡፡ ተከራዩም ‹‹አንተ ጠዋት ስትነሳ አገልጋዮቹን ስሩ ትላለህ፤ እኔ ግን ሰራተኞቹን ኑ እንሂድ እንስራ እላቸዋለሁ ምክንያቱ ይህ ብቻ ነው›› ብሎ መለሰለት፡፡

‹‹ሂዱ ስሩ በማለትና ኑ እንስራ በማለት መካከል ምን አይነት ልዩነት አለ›› ብሎ አሁንም ደግሞ ጠየቀው፡፡ ‹‹ልዩነቱማ አንተ ጠዋት ተነስተህ አገልጋዮችህን ሂዱ ስሩ ብለህ ትልካቸውና አንተ ጨዋታና

ፊንጠዝያ ወደ ሚገኝበት ቦታ እየሄድክ ገንዘብህንና ጊዜህን በከንቱ ስታባክን ትውላለህ። አገልጋዮችህ ደግሞ ጊዜያቸውን በማላገጥ ያሳልፉሉ እንጅ ምንም ስራ አይሰሩም። አንተም አጠገባቸው ሆነህ ስለማትመለከታቸውና ስለማትቆጣጠራቸው ልትቆጣቸው አትችልም። ስለዚህ ያንተ ጉዳት በሁለት በኩል ነው። በመጀመሪያ አንተ አትሰራም ደግሞም ገንዘብ ስታባክን ትውላለህ፤ ሁለተኛ አገልጋዮችህም ምንም አይሰሩም፤ ሰነፎች ናቸው። ታዲያ አንተ ያልከሰርክ ማን ይክሰር። እኔ ብትለኝ ግን ጠዋት በማለዳ ተነስቼ ኑ እንሂድ እንስራ ብዬ ሰራተኞቼን ከፊቴ አስቀድሜ እሄዳለሁ። እዚያ ስንደርስ በአጭር ታጥቄ በመካከላቸው ሆኜ እስከማታ እሰራለሁ። ሰራተኞ__ቼንም አብሬ በመሆን እቆጣጠራለሁ። እንደዚህ ሰርቼ እኔ ያላተረፍኩ ማን ያትርፍ ይኸውልህ ሂዱ ስሩ በማለትና ኑ እንሂድ እንስራ በማለት መካከል ያለው ትልቁ ልዩነት ይህ ነው። ›› አለው።

ከበደ ሚካኤል (1999) ታሪክና ምሳሌ 1ኛ መፅሃፍ፣ ገፅ 50-54 ተሻሽሎ የተወሰደ

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

### ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ።

1. የሰው ልጅ በዓለም ሲኖር ስራ የመስራት ግዴታ አለበት ትላላችሁ?
2. ሰውዬው መሬት እያለው ለኪሳራ የተዳረገው በምን ምክንያት ነው?
3. አብዛኛውን ጊዜ በጨዋታና ፈንጠዝያ ማሳለፍ ሊያስከትል የሚችለው ችግር ምንድን ነው?
4. ተከራዩ ሰውዬ የቀረውን መሬት እንዲሸጥለት የጠየቀው ለምን ፈልጎ ነው?
5. ባለመሬቱ ሰውዬ በሶስት ዓመት ውስጥ ያልተለወጠው በራሱ ነው ወይስ በሰራተኞቹ ችግር ይመስላችኋል? ምክንያቱን ለመምህራች ተናገሩ።

## ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. የመሬቱ ባለቤት እንዳላዋጣው ሲረዳ ምን አደረገ

   ሀ. ተጨማሪ መሬት ገዛ

   ለ. የቀረውን እኩሌታ ሸጠ

   ሐ. አንደኛውን እኩሌታ አከራየ

   መ. ለ እና ሐ መልሶች ናቸው

2. መሬቱን የተከራየው ሰውዬ መሬቱን ለምን ለምን ይጠቀምበት ነበር?

   ሀ. ለእርሻ　　ለ. ለአትክልት ስፍራ

   ሐ. ለከብት እርባታ　　መ. ሁሉም

3. ‹‹ባንተ መሬት ላይ ሰርቼ›› ያለው ማን ነው?

   ሀ. ተከራዩ　　ለ. ባለመሬቱ ሰውዬ

   ሐ. ሰራተኞቹ　　መ. ሁሉም

4. ‹‹ኑ እንሂድ እንስራ›› የሚለው አረፍተ ነገር ምን የሚል ሃሳብ ያስተላልፋል?

   ሀ. እናንተ ሂዱ እኔ እመጣለሁ፡፡

   ለ. አብረን በአንድ ላይ እንስራ ፡፡

   ሐ. ሰራተኞች ብቻ እንዲሰሩ መላክ፡፡

   መ. ለብቻ መስራት

5. ያንተ ጉዳት በሁለት በኩል ነው ያለው ምንና ምኑን ነው?

   ሀ. ሰውዬው ለራሱ አለመስራቱንና ገንዘብ ማባከኑ

ለ. አገልጋዮቹ ምንም አለመስራታቸው

ሐ. መሬቱን መሸጡንና ማከራየቱ

መ. ሀ እና ለ መልሶች ናቸው

6. በምንባቡ መሰረት አለመስራት ከሚከተሉት በምን ይገለፃል?

ሀ. ስኬታማ መሆን

ለ. ለችግርና ለድህነት በመጋለጥ

ሐ. ሃብት በማፍራት

መ. ረጂ በመሆን

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**ሀ. ተተኳሪ ቃላትን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን አሟሉ።**

ማሰላሰል፣ አመለካከት፣ ፈንጠዝያ፣ መስራት፣ ትጋት፣ ትርፋማ፣ ብድር

1. ሳምንቱን ምን መስራት እንዳለበት ተቀምጦ ጀመረ።
2. ሰውዬው በስራው ውጤታማ በመሆኑ ምክንያት ከልጆቹ ጋር ቀኑን በ________________አሳለፈ።
3. የሰው ልጅ ሰርቶ ለመለወጥ ለስራ ያለው____________አወንታዊ መሆን አለበት።
4. ወይዘሮ አስካለ በ______________ስለምትሰራ__________ ሆነች።
5. ከአቶ ካሳሁን____________ወስጄ የንግድ ስራ ጀመርኩ።

## ለ. የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ሀረጋትና አረፍተ ነገሮች በሃሳብ አብረው የሚሄዱትን መርጣችሁ አዛምዱ፡፡

ምሳሌ፡- በአግባቡ አልሰራም --ለድህነትተዳረገ

| ሀ | ለ |
| --- | --- |
| 1. ገንዘብ ያባክናል | ሀ. ተጨማሪ መሬት ገዛ |
| 2. መሬት ተከራየ | ለ. አትክልት አለማ |
| 3. ጠንክሮ ሰራ | ሐ. ለኪሳራ ተዳረገ |
| 4. ብዙ ገንዘብ አገኘ | መ. ውሳኔ ላይ ደረሰ |
| 5. በጥልቀት አሰበ | ሠ. ውጤታማ ሆነ |

**ተግባር ሶስት፡- መፃፍ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመመሪያው መሰረት በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. ‹‹ሰነፍ ይከስራል የሰራ ይከብራል›› በሚለው ሃሳብ ዙሪያ ሌሎች ተረቶችን ፈልጋችሁ በማንበብ የተረዳችሁትን ፍሬ ሃሳብ ፅፋችሁ ለጓደኞቻችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡
2. የቀረበላችሁን ምንባብ በድጋሚ በማንበብ ዋና ዋና ሃሳቦችን በአራት አረፍተ ነገሮች ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### ተግባር አንድ፡- በተመሳሳይ ሆሄ የሚጨርሱ ቃላት

**ሀ. በሚከተለው ምሳሌ መሰረት የመጨረሻ ቅርፃቸው ወይም ሆሄያቸው የሚመሳሰሉ ቃላትን ፃፉ፡፡ ለእያንዳንዱ ቢያንስ ሶስት ሶስት ቃላት ፃፉ፡፡**

ለምሳሌ፡- ሀ. ገነባ፣ ተቀባ፣ አዛባ

ለ. ተመታ፣ ሁካታ፣ ቸልታ

1. ቀመሰ ________ ________ ________
2. ከበረ ________ ________ ________
3. ቃረመ ________ ________ ________
4. ከፈለ ________ ________ ________
5. ጋረደ ________ ________ ________
6. ተከፋ ________ ________ ________

**ለ. በ<<ሀ>> ስር ለቀረቡት ቃላት ተስማሚ የሆኑትን ከ <<ለ>> ረድፍ መርጣችሁ አዛምዱ፡፡**

ምሳሌ፡- የእግር -- ሹራብ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የጣት | ሀ. ቤት |
| 2. የእጅ | ለ. ቀለበት |
| 3. ጥቁር | ሐ. መንገድ |
| 4. የሳር | መ. ሰዓት |
| 5. የአንገት | ሠ. ሹራብ |
| 6. የመኪና | ረ. ሀብል |

## ሐ. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

1. መለስተኛ
2. ደንታ ቢስ
3. ውዝግብ
4. ማሞገስ
5. ጭምት
6. ባለፀጋ
7. አደባ

## ክፍል አምስት፡- ጽሕፈት

### ተግባር አንድ፡- መፃፍ

1. እያንዳንዳችሁ በሳምንት ውስጥ የምትሰሯቸውን ስራዎች በቅደምተከተል በአምስት አረፍተ ነገሮች በፅሁፍ አስፍሩ።
2. ወደፊት ምን መስራት ትፈልጋላችሁ ወይም ምን መሆን ትፈልጋላችሁ? መስራት የምትፈልጉት ዓላማ ላይ ለመድረስ ምን ምን ተግባራትን ታከናውናላችሁ? የወደፊት እቅዳችሁን በስድስት አረፍተ ነገሮች በመፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- አያያዦች

### ሀ. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ተገቢውን አያያዥ ቃል ወይም ሀረግ በመምረጥ አሟሉ።

ነገር ግን፣ እንግዲህ፣ ምክንያቱም፣ ወይስ

1. በጠዋት ተነስቶ ነበር ______________ ከቤት አልወጣም።
2. ጫማ ______________ ልብስ ይሻልሻል?
3. በተደጋጋሚ ስመክረው ነበር ______________ ምንም ማድረግ አልችልም።

4. የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ትምህርት አመለጠው__________በሰዓት አልደረሰም፡፡

## ለ. የሚከተሉትን አያያዦች ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገሮችን መስርቱ።

1. ቢሆንም
2. አለበለዚያ
3. ይሁን እንጅ
4. ስለዚህ
5. ወይም
6. በስተቀር

**ተግባር ሁለት፡- ቅጥያዎች**

**ቅጥያዎች**

ቅጥያዎች በሶስት ይከፈላሉ፡፡ ከቃል በፊት የሚገቡ፣ ከቃል በኋሏ የሚገቡና በቃል መሃል የሚገቡ ናቸው፡፡

1. ከቃል በፊት የሚገቡት ለምሳሌ፡- ሀ. አስ- = አስመረቀ

ለ. እየ- = እየሄደ

ሐ. ሲ- = ሲመጣ

2. ከቃል በኋላ የሚገቡ ለምሳሌ፡- ሀ. -ኦች = ልጆች

ለ. -ኦችሁ = በሎችሁ

ሐ. -ዎች = በሬዎች

መ. -ኣን = መምህራን

3. በቃል መሀል የሚገቡ ለምሳሌ፡- ሀ. -ጫ- = አጫጭር

ለ. -ዠ- = ረዠዥም

ሐ. -ላ- = ወላለቀ

ወዘተ. የመሳሰሉት ቅጥያዎች ናቸው፡፡

## ሀ. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ቅጥያዎችን እየጨመራችሁ አጣምሩ፡፡

| ተ.ቁ | ዋና ቃል | -ኦች | -ኡ | -ኣችሁ | -ዋ | -ህ | -ኣችን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቅርስ | ቅርሶች | ቅርሱ | ቅርሳችሁ | ቅርስዋ | ቅርስህ | ቅርሳችን |
| 2 | ገንዘብ | | | | | | |
| 3 | ቤት | | | | | | |
| 4 | ዘመድ | | | | | | |
| 5 | ልብስ | | | | | | |
| 6 | ክፍል | | | | | | |
| 7 | አባት | | | | | | |

## ለ. ከሚከተሉት ቃላት ላይ የተጨመሩትን ቅጥያዎች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ለይታችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ንፁሃን፦ ዋና ቃል (ንፁህ) ሲሆን ቅጥያው (-ኣን) ነው፡፡

1. ቃላት
2. ቤታችን
3. ሰባበረ
4. ላሞች
5. ፈለጋችሁ

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. አንድ በአካባቢያችሁ የምታውቁትን በስራው ታታሪ የሆነ ሰው በምሳሌነት ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ።

2. ሰነፍ ይከሰራል የሰራ ይከብራል የሚለውን ምንባብ አንድ ጊዜ በየግላችሁ በለሆሳስ አንብቡ። ከዚያም የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ በራሳችሁ አገላለፅ በሶስት አረፍተ ነገሮች ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

3. ትምህርታችሁን ስትጨርሱ በምን ሙያ ላይ መሰማራት ትፈልጋላችሁ? የወደፊት እቅዳችሁን ግለፁ።

4. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ።

   ሀ. ብሂል

   ለ. ለሆሳስ

   ሐ. ተፈረጀ

   መ. በትር

5. የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም አረፍተ ነገር መስረቱ።

   ሀ. ስለዚህ

   ለ. እንጂ

   ሐ. ስለሆነ

አማርኛ

፫ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ዘጠኝ
# ባህል

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- በአዳመጣችሁት ምንባቡ ውስጥ የተነሱ ጉዳዮች ላይ ልምምድ ታደርጋላችሁ፡፡
- ምንባቡን አንብባችሁ መልዕክቱን ትረዳላችሁ፡፡
- በተሰጧችሁ ቃላት አረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- ለአዳዲስ ቃላት ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- በአረፍተ ነገር ውስጥ መስተዋድዶችን ትለያላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

### የአዲስ አመት በዓል አከባበር በኢትዮጲያ



**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ስዕሉን ስትመለከቱ ምን ተገነዘባችሁ?
2. አበባዎች ስታዩ ምን ታስታውሳላችሁ?
3. በአካባቢያችሁ የሚከበሩ ታላላቅ ክብረ በአላትን ዘርዝሩ

**ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መናገር**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት መልሱን በቃል ተናገሩ፡፡**

1. የእንቁጣጣሽ በዓል በየአመቱ መቼ ይከበራል?
2. በእንቁጣጣሽ ወቅት የሚሰጡ አበባዎች የምን መገለጫዎች ናቸው?
3. የራሷ የዘመን አቆጣጠር ያላት ሀገር ማን ናች?
4. በጥንት ጊዜ ኢፍ መስቀል እየተባለች የምትጠራዋ ምንድን ናት?
5. በሀገራችን የእንቁጣጣሽ በዓል የምን መገለጫ ነው?

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሃሳቡ ትክክል ከሆነ ''እውነት'' ካልሆነ ደግሞ ''ሀሰት'' በማለት በቃል መልሱ፡፡**

1. የሰው ዘር መገኛ ናት የተባለችው ኢትዮጵያ ናት፡፡
2. በአዲስ ዓመት መጀመሪያ ልጆች ለወላጆችና ለጎረቤት የምኞት መግለጫ ፖስት ካርድ ይሰጣሉ፡፡
3. ደመናማ ሰማይ የሚገፈፍበት የተባለው የነሃሴ ወር ነው፡፡
4. እውነተኛ እንቁጣጣሽ የሚለው ቃል ግጫ ነው፡፡
5. እንቁጣጣሽ በየሁለት ዓመቱ የሚከበር በዓል ነው፡፡

**ተግባር ሁለት፡- መናገር**

**በእንቁጣጣሽ ወቅት የሚዜሙ ወይም የሚባሉ ጨዋታዎችን አጥንታችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

**ተግባር ሶስት፡- ቃላት**

**ሀ. በ<<ሀ>> ስር ለተዘረዘሩት ቃላት ከ <<ለ>> ስር ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ጨለማ | ሀ. የሳር ዓይነት |
| 2. አውደ ዓመት | ለ. መታታት |
| 3. የምስራች | ሐ. ፅልመት |
| 4. ተንቆጠቆጠ | መ. የደስታ መግለጫ |
| 5. ኩልል | ሠ. አሸበረቀ |
| 6. እንግጫ | ረ. ክብረ በዓል |
| 7. ኮረብታዎች | ሰ. ጥርት |
| 8. መጎንጎን | ሸ. ጉብታዎች |

## ለ. የሚከተሉትን በ<<ሀ>> ረድፍ የቀረቡትን ቃላት በ<<ለ>> ረድፍ ካሉት ጋር ተቃራኒያቸውን በመፈለግ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የመጀመሪያ | ሀ. ተራራ |
| 2. ማሽብረቅ | ለ. ማደብዘዝ |
| 3. በዓል | ሐ. የመጨረሻ |
| 4. ሜዳ | መ. መጥፎ |
| 5. መልካም | ሠ. ንጥል |
| 6. ጥቅል | ረ. አዘቦት |

**ተግባር አራት፡- መፃፍ**

1. በአካባቢያችሁ በዓል ሲመጣ የሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦችን ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡
2. በአመት በዓል እለት የሚለበሱ ባህላዊ አልባሳትን ዝርዝር ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስደምጡ፡፡
3. አንድ የክብረ በዓል አከባበር ስርዓትን በመምረጥ ፅፋችሁ በመምጣት በክፍል ውስጥ ለመምህራችሁና ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍል ሁለት፣ - ንባብ

### ባህል



**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. ከስዕሉ የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. ባህል ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
3. በአካባቢያችሁ ሰርግ ሲኖር ምን ዓይነት ስነ ስርዓት ይከናወናል?

**ባህል**

ባህል ምንድን ነው ተብለን ብንጠየቅ ሁላችንም የተለያየ አይነት መልስ ልንሰጥ እንችላለን። እያንዳንዳችን የአንድ ማህበረሰብ አባል በመሆናችን ባህል አለን። ባህል የአንድን ማህበረሰብ ማንነት የሚያንፀባርቅ ነው። በሀገራችን በርካታ ብሄር ብሄረሰቦች ይገኛሉ። ሁሉም ብሄሮች የማንነታቸው መገለጫ ባህል አላቸው። ከነዚህም ውስጥ የጋብቻ ስነ ስርዓት፣ የለቅሶ ስነ ስርዓት፣ የልደት አከባበር ስርዓት፣ የአለባበስ ስርዓት፣ የተለያዩ የበዓል አከባበሮች፣ ከዓመት በአል ጋር ተያይዘው የሚዘጋጁ የተለያዩ ባህላዊ ምግቦች፣ በበአል ወቅት የሚለበሱ የተለያዩ አልባሳት፣ ባህላዊ የፀጉር አሰራር ፣ ለማጌጥ ወይም ለመዋብያነት የምንጠቀምባቸው ባህላዊ ጌጣ ጌጦች ሁሉ የባህል መገለጫዎች ናቸው።

## ባህል ለሰው ልጅ ምን አገልግሎት ይኖረዋል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ባህል ለማህበረሰባችን እንደ ህግ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ለምሳሌ፡-የእርቅና የለቅሶ ስርዓት ማንሳት እንችላለን፡፡ የእርቅ ስርዓት ሰዎች እርስ በርሳቸው ሲጣሉ የሚያስታርቁበት አንዱ መንገድ ነው፡፡ ከሁለቱም ባለጋራ ወገን ሽማግሌዎች ተቀምጠው ጉዳዩን ወደ ህግ አካላት

ሳይወስዱ በአካባቢያቸው በልምድ የሚጠቀሙበትን የግጭት አፈታት ህግ ተከትለው እርቀ ሰላም እንዲወርድ ያደርጋሉ፡፡ ይህ በሽምግልና ግጭት የሚፈታበት ስርዓት እንደየማህበረሰቡ ባህል የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡

ለአንድ ማህበረሰብ ሌላው የባህል መገለጫው የለቅሶ ስነ ስርዓት ነው፡፡ የሰው ልጅ በምድር ላይ ተወልዶ ሲኖር በርካታ የህይወት ምእራፎችን ያልፋል፡፡ ከነዚህ የህይወት ምዕራፎች አንዱና የመጨረሻው ሞት ነው፡፡ ሰው ሲሞት የቀብር ስርዓት ሲካሄድ ለቀስተኞች የአስከሬን ሽኝት የሚያደርጉበት መንገድ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ ለቅሶ ሲኖር የአካባቢው ሰውና ወዳጅ ዘመድ ተሰብስቦ ሃዘንተኛ ቤተሰብ ያጅባሉ፤ ያስተዛዝናሉ፡፡ አብረው በመገኘት የአስከሬን ሽኝት ያደርጋሉ፡፡ የሽኝቱ ስነስርዓትም እንደየማህበረሰቡ ባህል የተለያየ ነው፡፡

በአጠቃላይ ባህል ለአንድ ማህበረሰብ የማንነቱ ማንፀባረቂያ ብቻ ሳይሆን አንዱ ከአንዱ ጋር ህብር ፈጥሮ እንዲኖር የሚያስችል ነው፡፡ ባህል ከሰው ልጅ ጋር እጅግ የተቆራኘ ሀብት ነው ፡፡ የባህል ባለቤት መሆን የሚቻለው ደግሞ የማህበረሰብ አባል መሆን ሲቻል ነው፡፡ እያንዳንዱ ማህበረሰብም የራሱ ባህል አለው፡፡ ይህም የተለያየ የማህበረሰብ ባህል ደግሞ ብዙ ባህሎች እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡ በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያችን ባለብዙ ባህል ባለቤት በመሆን የታደለች ሀገር ናት፡፡

**ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ።**

1. የምንኖርበት ማህበረሰብ የራሱ ባህል አለው ትላላችሁ? መልሱን ለመምህራችሁ ተናገሩ::

2. ባህል እንዴት የማንነት መገለጫ ሊሆን ይችላል?

3. የባህል መገለጫ መንገዶች ምን ምን ናቸው? ዘርዝራችሁ ተናገሩ::

4. ሀገራችን ብዙ ባህል እንዲኖራት ያስቻላት ምንድን ነው?

5. እንደ ልደትና የሰርግ ስርዓት ያሉት የባህል መገለጫዎች ናቸው ማለት ይቻላል?

**ለ. ምንባቡንመሰረትበማድረግትክክልየሆነውንሃሳብ ''እውነት'' ስህተት የሆነውን ደግሞ ''ሀሰት'' በማለት በፅሁፍ መልሱ።**

1. ማንኛውም ማህበረሰብ የራሱ ባህል አለው::

2. ባህላዊ የፀጉር አሰራር የባህል ማሳያ ሊሆን ይችላል::

3. በባህላዊ መንገድ እርቀ ሰላም መፍጠር አይቻልም::

4. ማንኛውም ማህበረሰብ የተለያየ ባህል ቢኖረውም የሚያስተሳስረው አንዳች ነገር ግን አለው::

5. ባህል ከሰው ልጅ ጋር ብዙም ቁርኝት የለውም::

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**ሀ. ከዚህ በታች ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ።**

1. ባላጋራ

2. ባህል

3. ማሳያ

4. ህብር

5. መዋብያ

6. ማስታረቅ

## ለ. ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተቃራኒ ፍች ስጡ።

1. ውልደት
2. መቆራኘት
3. አንድነት
4. ሀዘን
5. ማውረድ

## ሐ. በሚከተሉት ቃላት አረፍተ ነገሮችን መስረቱባቸው።

1. ባህል
2. ሰላም
3. ማህበረሰብ
4. ይቻላል
5. አለው

**ተግባር ሶስት፡- መፃፍ**

1. በአካባቢያችሁ የለቅሶ ስርዓት እንዴት እንደሚከናወን ወላጆቻችሁን ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።
2. በአካባቢያችሁ ሰለባህላዊ የምርቃት ስነ ስርዓት ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ

ለምሳሌ፡- አባቶች ልጆችን ሲመርቁ የሚገልፅ


3. ልደታችሁን ስታከብሩ የምታደርጓቸውን ስርዓቶችን ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ።


## ክፍል ሶስት፡- ቃላት


### ተግባር አንድ፡- የቃላት ተመሳሳይ ፍች

**ሀ. በምሳሌው መሰረት ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ።**

ምሳሌ




2. መመንጠር
3. እንከን
4. አጠናቀቀ
5. ተገነዘበ

ለ. በ <<ሀ>> ስር ለቀረቡ ቃላት ከ <<ለ>> ስር ተቃራኒ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሸካራ | ሀ. ድርቅ |
| 2. መዘግየት | ለ. አነሰ |
| 3. ንፉግ | ሐ. መፍጠን |
| 4. ልምላሜ | መ. ለጋስ |
| 5. ገዘፈ | ሠ. ፈዛዛ |
| 6. ቀልጣፋ | ረ. ለስላሳ |

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ተግባር አንድ፡- መፃፍ

ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት በቅደም ተከተል በማስተካከል ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገሮቹን እንደገና አስተካክላችሁ ፃፉ።

1. ፅጌረዳ፣ ወንበር፣ ተቀመጠች፣ ላይ፣ ፀሀይ፣ አውጥታ
2. ወደቀ፣ ህፃኑ ልጅ፣ ተደናቅፎ፣ ሲሮጥ
3. ራቢያ፣ ተመረቀች፣ በጥሩ፣ ውጤት
4. ሂሩት፣ የሂሳብ፣ ሰራች፣ የቤት ስራ
5. ችግኝ፣ ሳዲቅ፣ ተከለ
6. ሙዚቃ፣ ያሬድ፣ ይወዳል፣ ማዳመጥ
7. እወዳለሁ፣ እኔ፣ መዝናኛ፣ መሄድ፣ ስፍራ

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- መስተዋድድ

**ማስታወሻ**

መስተዋድዶች ከስም በፊት ወይም በኋላ በመምጣት ስሙን ከሌላ ቃል ወይም ሀረግ ጋር የማዋደድ ወይም የማያያዝ

ተግባር አላቸው ::

መስተዋድዶች የሚባሉት፡- ስለ፣ እንደ፣ ከ፣ ለ፣ ወደ፣ አጠገብ፣ ባሻገር፣ ወዲህ፣ ላይ፣ ታች፣ ውስጥ ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው።

**ሀ. የሚከተሉትን መስተዋድዶች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ከስም ለይታችሁ አስምሩባቸው።**

ምሳሌ፡- ቤት አጠገብ = አጠገብ (ቤት ስም ሲሆን አጠገብ ደግሞ መስተዋድድ ነው።)

ከፒያሳ = ፒያሳ ( ከ መስተዋድድ ሲሆን ፒያሳ ደግሞ ስም ነው።)

1. ዛፍ ላይ
2. ስለትምህርት
3. ለወንድሙ
4. አዲስ አበባ ድረስ
5. ከወንዝ ማዶ
6. ወደትምህርት ቤት

**ለ. ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ መስተዋድድ የሆኑትን ቃላት ብቻ ለይታችሁ ፃፉ።**

ከ፣ ልጅ፣ ጥቁር፣ ወደ፣ ውስጥ፣ ምርኩዝ፣ ምንኛ፣ እንደ፣ ክብ፣ እስከ፣ ላይ፣ ትንሽ፣ ገዛ፣ አጠገብ፣ ቶሎ፣ ብልህ፣ ታች...

**ሐ. ከዚህ በታች የቀረቡትን መስተዋድዶች በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ።**

1. እስከ 2. አጠገብ 3.ድረስ 4.እንደ 5.ወዲህ

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በበዓላት ወቅት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የሚተላለፉ ባህላዊ ዝግጅቶች አዳምጣችሁ፤ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡
2. ከተለያዩ የበዓላት አከባበር ስርዓቶች ውስጥ አንዱን በመምረጥ ስለዚያ ባህል ጠይቃችሁ ወይም አንብባችሁ በመምጣት የተረዳችሁትን በፅሁፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡
3. ሁለት ሁለት ስምና ግስ የሆኑ ቃላትን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡
4. ለሚከተሉት ቃላት ሁለትና ከዚያ በላይ ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

    ሀ. ሰራ

    ለ. መንስኤ

    ሐ. አፀና

5. የሚከተሉትን መስተዋድዶች በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

    ሀ. እንደ

    ለ. ጋር

    ሐ. ስለ

    መ. ወደ

አማርኛ

፫ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አስር
# ገበያ

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የቀረበላችሁን ምንባብ አድምጣችሁ መልዕክቱን ትናገራላችሁ።
- በክፍል ደረጃችሁ ያነበባችሁትን ፅሁፍ ዋና ሀሳብ ታብራራላችሁ።
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ፍች ትሰጣላችሁ።
- አያያዥ ቃላት በመጠቀም ድርብ አረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ።

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

### ቅድስትና የገበያ ውሎዋ



**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. በስዕሉ ላይ ምን ምን ነገሮችን ተመለከታችሁ?
2. ከወላጆቻችሁ ጋር ገበያ ሄዳችሁ ታውቃላችሁ?
3. ገበያ ውስጥ ምን ምን ነገሮች ይገኛሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?

**ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።**

1. ባለታሪኳ ወደ ገበያ የሄደችሁ ምን ለማድረግ ነበር?
2. የቅድስት አማርኛ መምህር ምን ፅፋ እንድትመጣ አዘዟት?
3. ከከተማው ትንሽ ወጣ ብሎ ሰፊ ሜዳ ላይ ነው የተባለው ምኑ ነው?
4. ቅድስት ገበያ ለመሄድ ወላጆቿ አብረዋት ባይሆኑ ብቻዋን ትሄድ ነበር?
5. ባህላዊ የግብይት ስርዓት የሚባለው ምንድን ነው?

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሃሳቡ ትክክል ከሆነ <<እውነት>> ካልሆነ ደግሞ <<ሀሰት>> በማለት መልሳችሁን በቃል ተናገሩ። በምክንያት አስደግፋችሁ ግለፁ።**

1. ወላጆቿ የቅድስትን ጥያቄ ለመመለስ ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡
2. ቅድስት ገበያ ሄዳ የሚያስፈልጓትን ቁሳቁስ ሁሉ ገዛች፡፡
3. እነቅድስት የሄዱበት ገበያ ገዥና ሻጩ ያለ ክርክር ይገበያዩበት ነበር፡፡
4. በላስቲክ የተወጠሩት ሸራዎች ውስጥ ሸቀጦች በብዛት ይታዩ ነበር፡፡
5. ቅድስት ገበያ ውስጥ ማስታወሻዋን ትፅፍ የነበረው በግሏ ማጥናት ስለፈለገች ነው፡፡

**ተግባር ሁለት፡- መናገር**

**ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚከተለውን ጭውውት አጥንታችሁ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።**

ከዚህ በታች ነቢያት ሻጭ ነጋዴ ሆና የቀረበችበት፤ ይልቃል ደግሞ ገዥ ሆኖ ጭውውት ያረጉበት አጭር ጽሑፍ ቀርቧል፡፡ በሁለቱ መካከል የተደረገውን ምልልስ መነሻ በማድረግ እናንተም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ጭውውት አድርጉ፡፡

ነቢያት፡- የልብስ፤ የጫማና ሌሎችም የተለያዩ ነገሮች መሸጫ አላት፡፡
ይልቃል፡- ጫማ ይኖርሻል?
ነቢያት፡- አዎ! መምረጥ ትችላለህ፤ ቁጥር ንገረኝ፡፡ **ይልቃል**፡- ሰላሳ ስድስት ነው፡፡
ነቢያት፡- ይኸውልህ የተለያዩ ቀለም አማራጮች አሉኝ፡፡
ይልቃል፡- ጥቁር ጫማ ነው የምፈልገው፡፡ ነቢያት፡- አለ ዋጋው ሰባት መቶ ሃምሳ ብር ነው፡፡

**ተግባር ሶስት፡- ቃላት**

**ሀ. ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ።**

1. አድናቆት
2. ቅኝት
3. በተመስጦ
4. ዘገባ
5. ግብይት

**ለ. ለሚከተሉት በ<<ሀ>> ረድፍ ለቀረቡት ሀረጋት ተስማሚያቸውን ከ <<ለ>> ረድፍ እየመረጣችሁ አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሸቀጥ አከፋፋይ | ሀ. የመሸጫ ቦታ |
| 2. ሰፊ ሜዳ | ለ. ጅምላ ሻጭ |
| 3. የገበያ ተራ | ሐ. በተለምዶ የሚከናወን የንግድ ስርዓት |
| 4. ባህላዊ ግብይት | መ. የተንጣለለ መስክ |
| 5. የድንጋይ ካብ | ሠ. የመሸጫ መደብ |

**ተግባር አራት፡- መፃፍ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመመሪያው መሰረት በፅሁፍ መልሱ።**

1. በአካባቢያችሁ ወደሚገኝ ገበያ ከወላጆቻችሁ ጋር በመሄድ ባህላዊ የግብይት ስርዓቱ እንዴት እንደሚከናወን ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።
2. ባህላዊ የግብይት ስርዓት ከዘመናዊ የግብይት ስርዓቱ በምን እንደሚለይ በሰፈራችሁ አንድ የምታውቁትን ነጋዴ ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ። በፅሁፋችሁ ውስጥ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ መጠቀማችሁን አትርሱ።

## ክፍል ሁለት፦ ንባብ

### አዲስ አበባና የገበያ ቦታዎቿ



**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. በአካባቢችሁ የምታውቋቸውን የገበያ ስፍራዎች ጥቀሱ፡፡
3. ‹‹አዲስ አበባና የገበያ ቦታዎቿ›› የሚለው ምንባብ ስለምን የሚያስረዳ ይመስላችኋል?

### አዲስ አበባና የገበያ ቦታዎቿ

አዲስ አበባ የሀገሪቷ ዋና ከተማ እንደመሆኗ ከፍተኛ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ የሚታይባት ከተማ ናት፡፡ በከተማዋ ትላልቅ ዘመናዊና ባህላዊ የግብይት ስርዓቶች በስፋት ይከናወኑባታል፡፡ የተለያዩ የግብይት ቦታዎችም በብዛት አሏት፡፡ ዋና ዋናና ታዋቂ የግብይት ስፍራዎች ከሚባሉት ውስጥ እንደ መርካቶ፣ ሾሮ ሜዳ፣ ሾላ ገበያ፣ ካራና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

የመርካቶ ገበያ ግዙፍ የገበያ ቦታ ሲሆን ከጅምላ ማከፋፈያ አንስቶ እስከ ችርቻሮ መሸጫ ድረስ ሁሉም በአቅሙ የሚገበያይበት ቦታ ነው፡፡ መርካቶ ባህላዊና ዘመናዊ የግብይት ስርዓት በጥምረት የሚቀርቡበት ስፍራ ነው፡፡ በመሆኑም ከሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የሚመጡ በርካታ ነጋዴዎች የሚገናኙበት የገበያ ስፍራ ነው፡፡ ይህ ስፍራ ከፍተኛው የግብይት ስርዓት የሚካሔድበት በመሆኑ በአብዛኛው በገዥና ሻጭ ወይም በሰው ብዛት የተጨናነቀ ነው፡፡

ሌላኛው በከተማዋ የሚገኘው የገበያ ቦታ ሽሮሜዳ ነው፡፡ በውስጡም ሀገር በቀል የሆኑ ባህላዊ አልባሳት ይገኙበታል፡፡ ገበያው ውስጥ ገብቶ ግራና ቀኙን ለተመለከተ በተለያየ ህብረ ቀለማት ያሸበረቁት ባህላዊ አልባሳት ሳትገዙኝ አትለፉኝ የሚሉ ይመስላሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ አብዛኛውን ጊዜ ወደገበያ ስፍራ የገባ ሰው ሳይገዛ ባዶ እጁን አይወጣም፡፡ በእለቱ ገንዘብ ባይኖረው እንኳ ተመልሶ ለመሄድ ቀጠሮ የሚያዝለት የገበያ ስፍራ ነው፡፡

በከተማዋ በተለይ በዓመት በዓል ወቅት በእንስሳት ግብይት የሚታወቁ ቦታዎችም አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ የሾላ ገበያና ካራ ይጠቀሳሉ፡፡ የሾላ ገበያ ከእንስሳት በተጨማሪ የተለያዩ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ነገሮች በስፋት የሚገኙበት ነው፡፡ የሾላ ገበያ የተለያዩ የንግድና የፍጆታ እቃዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ይቀርቡበታል ከሚባሉ ስፍራዎች አንዱ ነው፡፡ በቁም እንስሳት ግብይትም ዶሮ፣ በግና ፍየል ከጠቦት እስከ ሙክት አቅሙ ለፈቀደ የእርድ በሬም የሚቀርብበት ገበያ ነው፡፡ የካራ ገበያም በስፋት በቁም እንስሳት ግብይት የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም በዓመት በዓል ዋዜማ የተለያዩ ለእርድ የሚውሉ የቁም እንስሳት ለማግኘት ወይም ለመግዛት ከተለያዩ የከተማዋ ክፍሎች ሰዎች በብዛት ወደዚያ ስፍራ በመሄድ ይገበያያሉ፡፡

**ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት**

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃል መልስ ስጡ።**

1. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚታወቁ ዋና ዋና የገበያ ቦታዎችን ዘርዝሩ::

2. አዲስ አበባ ውስጥ በትልቅነቱ የሚታወቀው የገበያ ቦታ የትኛው ነው?

3. የሸሮ ሜዳ ገበያ የሚታወቀው በምን የግብይት አይነት ነው?

4. ከምንባቡ የተረዳችሁትን ዋና ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ::

**ለ. በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆነ ''እውነት'' ስህተት ከሆነ ''ሀሰት'' በማለት መልሳችሁን በቃል ተናገሩ።**

1. ከጅምላ ማከፋፈያ እስከ ችርቻሮ ንግድ ሁሉም እንደአቅሙ የሚገበያይበት ቦታ መርካቶ ነው::

2. አዲስ አበባ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት ብቻ የሚከናወንባት ከተማ ናት::

3. ባዳመጣችሁት ምንባቡ ውስጥ በተጠቀሱት የገበያ ስፍራዎች በሁሉም ቦታ የቁም እንስሳት ብቻ ይሸጣሉ::

4. ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በመምጣት የሚገበያዩበት ትልቁ ቦታ ሾላ ገበያ ነው::

**ተግባር ሁለት፡- መናገር**

1. ወላጆቻችሁ ብዙ ጊዜ የሚገበያዩበትን ቦታ ጠይቃችሁ ምን ምን ነገሮች እንደሚሸጡ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ::

2. ገበያ የሚለውን ቃል ስትሰሙ በሃሳባችሁ የሚመጣውን ነገር በፅሁፍ ካዘጋጃችሁ በኋላ ለመምህራችሁ በቃል አቅርቡ::

**ተግባር ሶስት፡- ቃላት**

**ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡**

1. የተለያዩ የመገበያያ ስፍራዎች በከተማችን ውስጥ ይገኛሉ፡፡
2. መርካቶ ውስጥ የጅምላ ንግድ የተለመደ ነው፡፡
3. ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚመጡ በርካታ ነጋዴዎች አሉ፡፡
4. አብዛኛው የግብይት ስፍራ በሻጭና ገዥ የተጨናነቀ ነው፡፡
5. የካራ ገበያ በስፋት በቁም እንስሳት ግብይት የሚታወቅ ነው፡፡

**ተግባር አራት፡- መፃፍ**

1. መርካቶ ውስጥ ያሉትን የተራ ስሞች ወላጆቻችሁን ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
2. ወላጆቻችሁ ልብስ ወይም ሌላ ነገር ሲገዙ ከሻጩ ጋር ያለውን የዋጋ ክርክር ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

**ተግባር አንድ፡- ተቃራኒና ጥምር ቃላት**

**ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን በፅሁፍ ስጡ፡፡**

1. ቸኮለ
2. ዝምተኛ
3. ታላቅ
4. ተናወጠ
5. አዋደደ

**ማስታወሻ**

ልብ አድርቅ፣ ሆደ ሰፊ፣ ሰማይ ጠቀስ፣ ልብ ወለድ፣ ቃለ አጋኖ… የመሳሰሉት ጥምር ቃላት ይባላሉ።ጥምር ቃል ማለት ሁለት የተለያዩ ትርጉም ያላቸው ቃላቶች ተጣምረው የሚሰጡት አድስ ፍች ያለው ቃል ነው።

### ለ. በ<<ሀ>> ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ <<ለ>> ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እጀ ሰባራ | ሀ. ዋጋ አወረደ |
| 2. ዋጋ ሰባሪ | ለ. ባለጌ |
| 3. ስር ሰደደ | ሐ. ያልረባ ስራ |
| 4. ስመ ጥር | መ. ገናና፣ ዝነኛ |
| 5. አይን አውጣ | ሠ. ተጠናከረ |

### ሐ. በሚከተሉት ቃላት አረፍተ ነገር መስርቱ።

1. ወበቅ
2. ቀለብ
3. በረከት
4. ማዳከም
5. መዳረሻ

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ተግባር አንድ፡- መፃፍ

### የሚከተሉትን ጥያቄዎች በፅሁፍ መልሱ።

1. ‹‹አዲስ አበባ እና የገበያ ቦታዎቿ›› የሚለውን ምንባብ አንድ ጊዜ በጥሞና ደግማችሁ አንብቡ። ከዚያም የእያንዳንዱን አንቀፅ ዋና ሃሳብ ለይታችሁ አውጡ። ዋና ሃሳቡን በራሳችሁ አገላለፅ አብራርታችሁ ፃፉ። ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ መጠቀማችሁን አትርሱ።

2. በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ ወደሚገኝ አንድ የልብስ መሸጫ በመሄድ የዋጋ ዝርዝር ጠይቃችሁ ዘገባ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- አያያዦችን መለየት

**ሀ. በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን አያያዦችለይታችሁ አስምሩባቸው።**

1. አክስቴ እሁድ ወይም ሰኞ ትመጣለች።
2. ከባድ ዝናብ እየጣለ ቢሆንም ትምህርት ቤት መሄድ አለብኝ።
3. ገበያ የሄድኩት የዓመት በዓል ዶሮ ልገዛ እንጂ ልብስ ለመግዛት አይደለም።
4. ዛሬ ኳስ ጨዋታ ለማየት እሄዳለሁ፤ ስለዚህ ስራዬን በጊዜ መጨረስ አለብኝ።
5. ፈተና እየደረሰ ስለሆነ ሁላችንም ማጥናት የኖርብናል።

**ለ. ከዚህ በፊት በቀደሙት ምዕራፎች ያነሳናቸውን የቃል ክፍሎች ለማስታወስ ሞክሩ። ከዚህ በታች ስም፣ የስም ገላጮች፣ ግስ፣ የግስ ገላጮችና መስተዋድዶች ተደባልቀው ቀርበዋል። እያንዳንዳቸውን በየምድባቸው ለይታችሁ ፃፉ።**

ወደ፣ ክፉ፣ ቀጭን፣ ገነባ፣ ምንኛ፣ ናቸው፣ ልዑል፣ ግብርና፣ ቶሎ፣ አጠገብ፣ አስተዋለ፣ ሀብት፣ ያፌት፣ ገና፣ ስለ፣ ገመተ፣ እስከ፣ ንፉግ፣ ክፉኛ፣ የዋህ፣ አሁን፣ ላይ፣ ጎበዝ...

1. ስም
2. የስም ገላጭ
3. ግስ

4. የግስ ገላጭ

5. መስተዋድድ

**ሐ. የሚከተሉትን ያልተሟሉ አረፍተ ነገሮች በተገቢው ቃል አሟሉ።**

አነበበ፣ ስለ፣ እስከ፣ ገበያ፣ አንብቡ፣ ጎበዝ፣ ጥቁር፣ በፍጥነት

1. ______________ የተለያዩ ነገሮች የሚሸጡበት ቦታ ነው፡፡

2. አየለች ከቤት____________ወጣች

3. በመማሪያ መፅሃፍ ላይ ያለውን ምንባብ በየግላችሁ________

4. ______________ነጋዴ በመሆኑ ትልቅ ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡

5. ከቤታችን____________ትምህርት ቤት ድረስ በእግሬ መጣሁ፡፡

**መ. የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት ወይም ሀረጋት በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

1. ሆኖም

2. ነገር ግን

3. ይሁን እንጅ

4. ወይም

5. እና

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ባህላዊና ዘመናዊ የግብይት ስርዓትን በተመለከተ በቴሌቪዥን የሚተላለፉ ዘገባዎችን አድምጣችሁ በማስታወሻችሁ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተርኩላቸው፡፡

2. ስለሻጭና ገዥ የሚያነሱ ፅሁፎችን ፈልጋችሁ አንብቡ፡፡ ያነበባችሁትን ፅሁፍ ዋና ሀሳብ በማስታወሻ ደብተራችሁ በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

3. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

    ሀ. ውጥረት

    ለ. መጠጊያ

    ሐ. እንደልብ

    መ. ባለጠጋ

4. የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም ድርብ አረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡

    ሀ. ቢሆንም

    ለ. ስለሆነም

5. የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም አረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡

    ሀ. ግን

    ለ. ወይስ

    ሐ. ከዚያም

# የቃላት ፍቺ

| ቃል | ፍቺ |
|---|---|
| ሀያል | ጠንካራ፣ የማይሸነፍ፣ ብርቱ፣ ሀይለኛ |
| ሁነኛ ሰው | ታማኝ፣ ሀቀኛ፣ ተስማሚ |
| ህመም | በሽታ፣ ደዌ፣ ጤና ማጣት |
| ህብረት | መረዳዳት፣ መተባበር፣ መተጋገዝ |
| ለማ | በለፀገ፣ ለመለመ |
| መለገሰ | መለገስ፣ መቸር፣ መስጠት |
| መሄድ | መራመድ፣ መገስገስ |
| መላ | ዘዴ፣ ብልሃት፣ ማስተዋል |
| መመኘት | መከጀል፣ መሻት |
| መስማማት | መዋደድ፣ ማዋዋል፣ ማደራደር |
| ርህራሄ | አዘኔታ፣ ቸርነት፣ ደግነት፣ መራራት |
| ሰበብ | ሳቢያ፣ ምክንያት፣ መንስኤ |
| ስነ-ጥበብ | ስዕል፣ ቅርፃ ቅርፅ፣ ሙዚቃ፣ ስነ ፅሁፍ |
| ቀረበ | ተጠጋ፣ ለመድረስ ትንሽ ቀረው |
| ቀየረ | ለወጠ፣ ተካ፣ አዛወረ፣ |
| ብልሹ | የማይረባ፣ የማይጠቅም |
| ባህል | ልማድ፣ ወግ |
| ተመቸ | ደላ፣ ተስማማ፣ ምቹ ሆነ |
| ተሰናኘ | ተስማማ፣ ተገጣጠመ |
| ተቀኘ | ደረሰ፣ አሰበ |
| አመለከተ | አሳየ፣ አስረዳ፣ ጠቆመ |
| አስተናገደ | ተቀበለ፣ አበላ፣ አጠጣ፣ ጋበዘ |
| ከመረ | ቆለለ፣ ደረደረ፣ አነባበረ |
| ከረከመ | አሳጠረ፣ አስተካከለ፣ ቀረጠፈ |
| ውበት | ቆንጆ፣ ያማረ፣ ደምግባት |
| ውድድር | ፉክክር፣ ክርክር፣ ውርርድ |
| ጨመቀ | ጠመዘዘ፣ አንጠፈጠፈ |
| ፀጋ | ሀብት፣ ስጦታ፣ ረደኤት |
| ፈፀመ | ጨረሰ፣ አጠናቀቀ፣ ሰራ፣ አደረገ |

# ዋቢ ጽሑፎች


ቅድስት ማርያም ዩኒቨርሲቲ። (1995)። ስነ ቃል። አዲስ አበባ፣ ያልታተመ።

በላይነሽ የሻው እና ቢረሳው ታደሰ። (2010)። አማርኛ 3ኛና 4ኛ ክፍል። አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት።

ባህል ወ ቱሪዝም። (2008) አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ቅፅ 7፣ ቁጥር 12፣ 7-8።

ባህሩ ዘርጋው (2010) ዘርጋው መለስተኛ መርጃ መዝገበ ቃላት (2ተኛ እትም)። አዲስ አበባ ሮሆቦት አታሚዎች

ባየ ይማም። (2004)። አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው። አዲስ አበባ፣ አልፋ ፕሪንተር።

ተስፋ ገብረስላሴ(ዓም ያልታወቀ) የአማርኛ ፊደለ ገበታ።

አላምረው ገብረ ማርያም (2002) አማርኛ መማሪያ መፅሀፍ 1-4ኛ ክፍል። አዲስ አበባ፣ አልታ ማተሚያ ቤት።

አስምረት ብስራት (2013) የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች። አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ዌብሳይት ኢአይ የተወሰደ።

አብርሃም እንዳሻው (ዓ/ም ያልተጠቀሰ) ኢትዮጲስ ቁጥር 2 አዲስ ዘመን (2013) የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት።

ከበደ ሚካኤል (1999) ታሪክና ምሳሌ ።1ኛ መፅሃፍ፣አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ደርጅት።

ፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣንና ትምህርት ሚኒስቴር (2011) የትምህርት ቤቶች የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ክበባት አደረጃጀትና አሰራር። ንቁ በርታ ማተሚያ ቤት።

ደበበ ሀ/ጊወርጊስ (2005) ሳባ የአማርኛ መዝገብ ቃላት ሰናትኛ እትም አዲስ አበባ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት

(2011) የተማሩት እህትማማቾች። አዲስ አበባ፣ USAID- READ II PROJECT።

ዳንኤል ወርቁ (2011) የዛፎች ጠላት ማን ነው። አዲስ አበባ።

USAID- READ II PROJECT USAID (2019) የሀና ጊዜ አጠቃቀም:: አዲስ አበባ፣ READ II PROJECT::

USAID (2019) የመጓጓዣ አይነቶች :: አዲስ አበባ፣ READ II PROJECT::

USAID (2019) የቅድስት ውሎ ዘገባ:: አዲስ አበባ፣ READ II PROJECT::

## • የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሳልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

## የፊደል ቅደም ተከተል

ሀ የመጀመሪያ ፊደል = ገዕዝ

ሁ ሁለተኛ ፊደል = ካዕብ

ሂ ሶስተኛ ፊደል = ሳልስ

ሃ አምስተኛ ፊደል = ሳድስ

ህ ስደስተኛ ፊደል = ሳብዕ

## • የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| ከ1 እስከ 10 | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፩ | 1 |
| ፪ | 2 |
| ፫ | 3 |
| ፬ | 4 |
| ፭ | 5 |
| ፮ | 6 |
| ፯ | 7 |
| ፰ | 8 |
| ፱ | 9 |
| ፲ | 10 |

| ከ11 እስከ 20 | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፲፩ | 11 |
| ፲፪ | 12 |
| ፲፫ | 13 |
| ፲፬ | 14 |
| ፲፭ | 15 |
| ፲፮ | 16 |
| ፲፯ | 17 |
| ፲፰ | 18 |
| ፲፱ | 19 |
| ፳ | 20 |

| ከ20 እስከ 100 | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፳ | 20 |
| ፴ | 30 |
| ፵ | 40 |
| ፶ | 50 |
| ፷ | 60 |
| ፸ | 70 |
| ፹ | 80 |
| ፺ | 90 |
| ፻ | 100 |

| ከ100 እስከ 1000 | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፻ | 100 |
| ፪፻ | 200 |
| ፫፻ | 300 |
| ፬፻ | 400 |
| ፭፻ | 500 |
| ፮፻ | 600 |
| ፯፻ | 700 |
| ፰፻ | 800 |
| ፱፻ | 900 |
| ፲፻ | 1000 |

| ከ2000 እስከ 10000 | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፳፻ | 2000 |
| ፴፻ | 3000 |
| ፵፻ | 4000 |
| ፶፻ | 5000 |
| ፷፻ | 6000 |
| ፸፻ | 7000 |
| ፹፻ | 8000 |
| ፺፻ | 9000 |
| ፼ | 10000 |

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## ፫ኛ ክፍል


አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU